ጥላ /የካቲት 2006 ዓ.ም ሁለተኛ ዓመት ቁ.9 Tila February 2014 2nd year 9th edition



Senator Dr. Patrick Leahy
USA Congress President

# አራተኛው ሰው ጉድ አፈሉ!

# Ethio-Sudan Border: Behind the curtain

**Tila Editorial**





ጥላ
TILA
ጥላ የካቲት 2004 ዓ.ም አንደኛ ዓመት ቁ 1 TILA February 2012 First Year 1st Edition
ወያኔን ያናጋው የአኮግ ውሳኔ!!
Harassment tool – Ethiopian anti Terrorism Law
ዛምቢያ—የአፍሪካ ዋንጫ ንጉስ



ጥላ
TILA
ጥላ ግንቦት 2004 ዓ.ም አንደኛ ዓመት ቁ 2 TILA May 2012 First Year 2nd Edition
በፖለቲካችን ሁሉም አትሌት መሆን ነው ያለበት!!
አዲሶስ ሮሜሲ!
No More Joseph Konys!!
uefa champions league finale



ጥላ
TILA
Where is The Ethiopian Prime Minister? WANTED!
The Sugar Candy Mountain



ጥላ
TILA
TILA November 2012 First Year 4th Edition
ሰው ጥራ ቢሉት ራሱ መጣ !
We need a regime change not……
funny but true




ጥላ
TILA
ጥላ ጥር 2005 ዓ.ም 1ኛ ዓመት ቁ 5 ልዩ እትም TILA January 2013 1st Year 5th Spe. Edition
በኢ.ህአዴግ ውስጥ የተፈጠረውን ክፍተት ልንጠቀምበት ይገባል።
አቶ ግደይ ዘርዓፅዮን
"የኢ.ህአዴግ ተቃዋሚ መሆን የመናገር መብትን ያስከለክላል፤ የኢ.ህአዴግ አባል መሆን ደግሞ የማሰብ ነጻነትን ያሳጣል።"
An opposition member has no right to speak; while
An EPRDF member has no right to think.
CONFEDERATION AFRICAINE DE FOOTBALL



ጥላ
TILA
ጥላ ግንቦት 2005 ዓ.ም 2ኛ ዓመት ቁ 6 TILA May 2013 2nd Year 6th Edition
Free
የኢትዮጵያ ፕሬስ ነፃነት ተምሳሌት ርዕዮት ዓለሙ



ጥላ
TILA
ጥላ ነሐሴ 2005 ዓ.ም 2ኛ ዓመት ቁ 7 TILA August 2013 2nd Year 7th Edition
አባይ ሊያለማን ወይስ ሊያጠፋን?
አዲሱ የጥላ አድራሻችን
Mesfin Abraha
An der Obergeis 1
36251 Bad Hersfeld
በሞቃዲሹ የተከሰከሰው የኢትዮጵያ አውሮፕላን
03-12-2005 ዓ.ም
የአግአዚው ሻንዳም -ኮፈሌ



ጥላ
TILA
ጥላ /ህዳር-ታህሳስ 2006 ዓ.ም ሁለተኛ ዓመት ቁ.8 Tila Nov/Dec 2013 2nd year 8th edition
መንግስት- ስደት—ውርደት

# ጥላ

ዋና ስራ አስኪያጅ General Manager

መስፍን አብርሃ Mesfin Abraha

ዋና አዘጋጆች Editor In Chiefs

እየሩሳሌም ሱሞሮ Eyerusalem Sumoro

ዳዊት ፋንታ Dawit Fanta

ደሳለኝ አበበው Desalegne Abebew

አዘጋጆች Editors

ዮሃንስ ሳምሶን Yohanes Samson

ደበበ ከበደ Debebe Kebede

ፍስሃፅዮን ሃይለገብርኤል Fisshatsion Hailegeberile

ጽሁፍ አስተባባሪዎች Coordinators

ብርሃኑ ባዩ Berhanu Baue

ኤደን ዳዊት Eden Dawit

አስናቀች ጥላሁን Asnakch Telahun

በተወዳጅ አድነው Betewedaj Adenew

የኮምፒዩተር ፅሁፍ ቅንብር Computer Graphics

ህሊና ዳዊት Hilina Dawit


የጥላ መጽሔት አድራሻ/Tila Magazine Address

Mesfin Abraha

An der Obergeis 1

36251 Bad Hersfeld

Email:- tilamagazine@yahoo.de

Web-Site:- tilamagazine.yolasite.com

Tel.No.:- 015222195567, 017659384456, 017671668780

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| አራተኛው ሰው ጉድ አፈሉ | 8 |
| በፕሬስ አፈና ግንባር ቀደም አገር | 10 |
| ሉዓላዊነታችን ይከበር | 10 |
| የአገራችንን ድንበር አናስደፍርም! | 10 |
| ዝምታችን ይብቃ! | 11 |
| መሬት ቆርሶ መሸጥ ..... | 12 |
| የፍርድ ቤት ባርነት... | 12 |
| ለህሊና ማደር | 13 |
| አዲሱ ሃይማኖት | 13 |
| የፕሬስ መብት- እንዴት? | 14 |
| ሰላም ስነ-ግጥም | 14 |
| እምየ ኢትዮጵያ | 15 |
| አንቺ አገሬ | 17 |
| ከሱዳን ጋር የተደረገው | 18 |
| Justice | 20 |
| Democracy … | 21 |
| We can reconcile | 21 |
| We need ….. | 21 |
| Land grabs and … | 22 |
| Struggle for … | 22 |
| Unity is power | 22 |
| Free prisoners … | 22 |
| Love is the … | 23 |
| Stop land … | 23 |
| National … | 24 |


**መልካም ንባብ**

**ጥላ መጽሔት**

## Where the press is free and every man able to read, all is safe.

**Thomas Jefferson**

# ABOUT TILA

**R**ealizing the fact that the digital age has empowered and made ordinary people across the world irrepressible beyond their imagination, **WE** aims to serve as a credible platform that will spread uncensored interviews, news, commentaries and analyses that are unlikely to see daylight in Ethiopia.

Fortunately, here is where you find **TILA**, the un-disputably best source of information serving the Ethiopian Diaspora community in Europe & America with a proven record of excellence in journalism.

**TILA** is a political magazine published and distributed by patriotic Ethiopians around Hessen region in Germany. **Tila** appears in Amharic, English and Germany Languages every 3 months. It is a magazine of quality, responsibility and standard. Entertainment and sport are among our coverage issues next to Ethiopian politics.

As a reader, you are to get useful political and current news in **TILA** than any other publication can offer you. More comprehensive analysis and interpretations than any other media can present to you. In fact, these are some of the qualities of **TILA** that has made it the largest circulating magazine in its category. **TILA** magazine has also partnered with ethiomedia.com, ethiogermany.de, ethiopiazare.com and afroaddis.wordpress.com, goolgule.com among others, to deliver reliable and high quality content to our visitors. The articles which are posting here doesn`t represent the Magazine`s Editorial committee, rather the writers.

Don't take the chance of missing this spectacular political magazine. Subscribe to it today! We promise, you won't regret your decision. Reach us on tilamagazine@yahoo.de & tilamagazine.yolasite.com

## Tila Magazine is yours Magazine!


## ውድ አንባብያን

ጥላ መጽሔት በየሶስት ወሩ የሚታተም የፖለቲካ መጹሔት ነው።መጽሔቱ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሰረት አድርጎ በጀርመን አገር የሚታተም ቢሆንም መረጃ መረቦችን በመጠቀም መላውን ዓለም የማዳረስ ዓላማን አንግቦ እየተንቀሳቀሰ ነው።

የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታና ጠቃሚ መረጃዎችን በማካተት ዝናን ያተረፈው የጥምረት መጽሔት አዘጋጆች ያቋቋሙት ጥላ መጽሔት የስሙ ስያሜ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተበታተነ ሁኔታ የሚያካሂዱትን የትግል ሂደት በማስቀረት በአንድ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ ለማሳሰብና አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

የፖለቲካ ሃይሎች በተበታተነ ትግላቸው ጋት እንኳን መራመድ እንደማይችሉ በመገንዘብ የጋራ ትግል እንዲያካሂዱ ለማበረታታትም ጭምር ነው እ.ኤ.አ ከጥር 2012 ጀምሮ በዚህ ስም መጽሔቱ እንዲጠራ የወሰንነው።በመጽሔቱ አዝናኝና አስተማሪ ዝግጅቶች የሚካተቱበት ሲሆን ስፖርትም ትኩረት ያገኛል። ጥላ መጽሔት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን ያለምንም ገደብ በነፃነት የሚያቀርብበት ክፍት መድረክ በመሆኑ በመጽሔቱ የሚወጡት ፅሁፎች በሙሉ የፀሃፊዎቹን እንጂ የጥላ መጽሔት ዝግጅት ክፍልን የማይመለከቱ መሆናቸውንም መግለፅ እንወዳለን።

**ጥላ መጽሔት የእናንተው መጽሔት ናት!**



# ርዕሰ አንቀጽ



## የኢትዮ-ሱዳን ድንበር፡ከመጋረጃ በስተጀርባ

ድንበሮች የሚወሰኑት በመሬት አቀማመጥ በፖለቲካ አስተሳሰብ በዜግነት በቋንቋና በባህል መለኪያዎች ነው።አንዳንድ ጊዜ በግልፅ መለኪያዎቹ ሲቀመጡ ሌላ ጊዜ ምናባዊ ይሆናሉ።ነገር ግን መለኪያዎቹ በአካባቢው ተደራሽ ለሆኑት ህዝቦች እጅግ በጣም ጠቃሚዎች ናቸው።በጦርነት ወቅት ድንበሮች ዘወትር ግልፅ አይደሉም።ምክንያቱም እዚህ ግባ የሚባል አከላለል የተደረገላቸው ባለመሆናቸው። የድንበር ወሰኖች ስምምነት የሚፈፀመው በመንግስታት መሪዎች በመሆኑ ለዘመናት የዘለቁ የአለመስማማት መንስኤዎች ይሆናሉ። ድንበሮች ሲለወጡ በአካባቢው ያሉትን ህዝቦች ዜግነትና የንግድ ብሎም የአገልግሎት ተግባራት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ።

ድንበሮች ከካርታ አልፈው መሬት ላይ በችካል እስካልተቸከሉ ድረስ የአንዱ ድንበር የት እንደሚጀምርና ሌላኛው የት እንደሚያልቅ ለማወቅ ያስቸግራል።ድንበሮች በተለይ ከባህር ጋር የተያያዙ ከሆነ ለአከላለሉ ትልቅ እንቅፋት ይሆናሉ።ከፍተኛ ስፋትና አገር አቋራጭ ባህሮች ላይ ድንበር የሚባል ነገር አይነሳም።


የ1990 ዓ.ም የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር ጦርነት በእውነት ማንም ያላሸነፈበት ነበር? ይህ ጥያቄ ጦርነቱ በኦፊሴል ከተጠናቀቀበት 1992 መጨረሻ ጀምሮ መከራከሪያ ነጥብ ሆኗል።በምክንያትነት የሚጠቀሰውም ሁለቱም ወገኖች አንደኛው በሌላኛው ላይ ስትራቴጂካዊ ድል አለመጎናፀፉን ነው።ከጦርነቱ በሁዋላም የተለወጠ ድንበር የለምና።የታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚሉትም በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ለእልቂት የተዳረጉት ዋናዎቹ አህጉር በቀል ነዋሪዎች ናቸው።ለጥቂት የፖለቲካ ትርፍ ተብሎ ዜጎቹ ለዚህ መዳረጋቸውም በከፍተኛ ኪሳራነት ሳይጠቀስ አያልፍም።ጦርነቱ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብና ከ150 ሺ በላይ ህይወትን የቀረጠፈ መሆኑም አይዘነጋም።

እኛ ኢትዮጵያውያን የድንበር ጦርነት ምን እንደሚመስል ውጫዊ ማስረጃ አያስፈልገንም።እኛው ከበቂ በላይ ልምድ አለንና።ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግስት በኢትዮ-ሱዳን ድንበር ስምምነት ዙሪያ ከመጋረጃው በስተጀርባ የሚያካሂደውን ድርድር ለህዝቡ ይፋ ማድረግ አለበት።

ጥርጣሬዎች ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰዋል።በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት የተፈፀመውን አይነት ስህተት መድገም ተቀባይነት የለውም።የሱዳን ባለስልጣናት በስምምነቱ መደሰታቸውን እየገለፁ ነው።ለምን ደስተኛ ሆኑ?ለህትመት እስከምንገባበት ቀን ድረስየታወቀ ነገር የለም።ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግስት በጉዳዩ ዙሪያ ግልፅ መሆንና ስምምነቱ ወደ ጦርነት የማይወስደን መሆኑን ሊያረጋግጥልን ይገባል።አራት ነጥብ።የኢትዮ-ሱዳን ድንበር በቀድሞ ቅኝ ገዢዎች በነበሩት በእንግሊዝና በኢጣሊያ አማካኝነት በ1900ዓ.ም መፈፀሙ የሚታወስ ነው።

እንደተለመደው ጥላ መጽሔት ወቅታዊ ጉዳዮችን ዳስሳ ይዛላችሁ ቀርባለች።መልካም ንባብ ይሁንላችሁ።

**ጥላ መጽሔት የእናንተው መጽሔት ናት!**



# EDITORIAL



## Ethio-Sudan Border: Behind the curtain

**B**orders are defined in geographic, political, national, linguistic and cultural terms. Sometimes they are clearly defined and other times they are abstract, though still significant to the populations affected by them. During Wars, borders were often unclear as no proper survey had been done to define the boundaries. Border decisions were made by government leaders and frequently led to decades of disagreements. When borders changed, they often affected the people living on either side by determining their nationality and their ability to trade for goods and services.

Unless a border is identified by a physical landmark, it is often difficult to see where one territory ends and another begins. When borders fall in the middle of large bodies of water, they become even less clear. In the open seas, there are no borders.

Was the War between Ethio-Eritrea of 1998 really the war nobody won? This question has been debated since the war ended in 2000. Part of the reason for debate is that neither side achieved a strategic victory over the other. By the end of the war, no borders had changed from the pre-war period. Many historians agree that the group who lost the most in the War of 1998 was the continent's Aboriginal peoples, who incurred major losses with very little political gain.The war claims a billions of money and above 150,000 people.

We, Ethiopians don`t need any foreign example what seems a border war like. We have a lot of experiences. So, the Ethiopian government should have to release facts about the behind curtain agreement with its Sudanese counterpart.


Speculations are very high now. We don`t need the same mistake, what you people are doing with Eritrea. We are confirmed, that the officials of the Sudanese government are very happy with the so called agreement. Why are they happy? We don`t know recently. But the government of our side should have to be transparent. And assure us the agreement will never take us to war! Period.

The borders between Ethiopia and Sudan were drawn by the British and Italian colonizers in 1908.As always Tila wish you a nice reading.

**TILA MAGAZINE IS YOURS MAGAZINE !**

# Ethiopia which was kept autonomous by our ancestors will ever remain autonomous by its present generation!!!

**Desalegne Abebew Syit &Yalemwork Meswaet/Schöneck-Kilianstädten**




***Those who dismantled and trying to dismantle Ethiopia, that was kept united by our fathers, will never escape from accountability either historically or physically.***

Ethiopia is a country with the largest population in Africa second to Nigeria and it is also the only country in Africa which remained uncolonized during the colonization era. Historically colonizers were unable to invade Ethiopia and also Eritrea before its secession. But in recent time, withdrawal of Eritrea was done only by the agreement of the leaders of the two countries without involving participation of their people. In 1989, the TPLF reached agreement with Eritrea on handing over Assab to Eritrea. By this decision, Meles Zenawi singlehandedly reduced Ethiopia from a historical country with two ports to status of being landlocked.

Finally, the dispute on demarcation of the border led to the 1998-2000 war between the two most poverty-stricken states of the planet.

Afterwards, TPLF continued to hand over part of the fertile land of Amhara region called Humera to Tigrean people and to Sudan. The previous president and vice president of Amhara region called Mr. Ayalew Gobeza and Mr. Demeke Mekonnen had been involved during this occasion.

Like the Port of Assab that Meles awarded Eritrea, huge agricultural lands in Amhara region have been passed on to Sudan step by step. Currently, TPLF had signed the agreement with Sudan government to give extra productive land of Amhara region called `Fashaga` and the size is confirmed to be 1600km in length and 40km in width.

According to the news from Sudan Tribune, the handover will be carried out on March 30, 2014 by providing the reason that the colonial border between Northern Sudan and Ethiopia was not demarcated.

Regarding the border, they have no any historical evidence which can indicate the demarcation drawn by representatives of the two countries except the one that was drawn by the British and Italian colonizers in 1908. On the side of Ethiopia, either TPLF officials or its media has not tried to inform the people regarding this issue and they continued keeping it secrete. They agreed to resolve all their border demarcation disputes only by themselves without discussion with Ethiopian people.

On the other hand, this is their mechanism designed to get geo-political benefit and to increase their shelf-life in power. There is no any possibility of clearly understanding of the nature and behavior of the TPLF regime. Whenever it is in trouble, it has been known to be putting everything on fire sale. Its aim is to merely jump as quickly as possible to safer ground.

TPLF became willing to erode the sovereignty and national territorial integrity of an autonomous country (Ethiopia) due to the following reasons or realities:

- To accomplish their promise they gave for the treaty of Sudan`s help during their previous fighting time.
- To make the Amhara ethnic group weak and fragile by displacing them from their fertile agricultural land.
- To block the entrance of opposition forces through the border of Sudan. TPLF was selling the disputed lands to Sudan in return for peace on the common border. Therefore, Sudan will not allow its territory to be used by anti-TPLF armed groups.
- To get the support of Sudan as tensions persist with Egypt over a giant renaissance dam. Due to this argument, TPLF will give also 100 kilowatt power of electricity to neutralize the Sudan over the dam.
- To get access to Port Sudan when the Tigrean region become departed from Ethiopia, according to their long term plan.

Consequently the following things will happen soon: Lack of integrity of the country, farmers will be subjected to attacks during their resistance to take over their territory, war will be opened between Sudan and Ethiopia. In general, security of East Africa will be affected.

Therefore, any Ethiopians who think for his country and also all international community should give advice and make them stop from this miscalculated action of the dictatorial regime of Ethiopia.

Justice and freedom for our beloved country Ethiopia!!!

# አራተኛው ሰው ጉድ አፈሉ!

**ጋዜጠኛ መስፍን ኣብርሃ/ ከጥላ መጽሔት ዝግጅት ክፍል**

ኢትዮጵያና አሜሪካ የሁለትዮሽ ግንኙነታቸውን ከጀመሩ ዘንድሮ 111ኛ ዓመታቸውን ይዘዋል።በቀድሞው የኢትዮጵያ ንጉስ አፄ ምንሊክና በአሜሪካው አቻቸው ፕሬዚዳንት ቴዎዶር ሩዝቬልት ልዑካን መካከል ለዘጠኝ ቀናት ድርድር ከተካሄደ በሁዋላ ነበር ግንኙነቱ በይፋ የተጀመረው።ከአንድ ክፍለ-ዘመን በላይ ያስቆጠረው የአገራቱን ግንኙነት በመጠቀም ኢትዮጵያ ጠቀም ያለ እርዳታዎችን ተቀብላለች።በአሁኑ ወቅትም በየዓመቱ ከ500 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የልማትና የወታደራዊ እርዳታ ተጠቃሚ ናት። አሜሪካም ብትሆን ፖለቲካዊ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ከአገራችን ታገኛለች።


ሆኖም ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ አሜሪካ በኢትዮጵያ ባሉ የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ዙሪያ ቅር መሰኘታን ደጋግማ ስትገልፅ ቆይታለች።በየዓመቱ በአሜሪካ መንግስት ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚወጣው የአገራት የሰብዓዊ መብት ሪፖርትም ኢትዮጵያ ባላት ሪከርድ በአሜሪካ ክፉኛ ስትተች ነበር።
ይህን ተከትሎም ይመስላል የአሜሪካ ህግ አውጪ ምክር ቤት/ኮንግረንስ ጥር 7/2006 ዓ.ም ባወጣው ዓመታዊ የበጀት ድልድል ቀመር ለኢትዮጵያ በሚሰጠው የልማትና ወታደራዊ ድጋፍ ላይ ቅድመ ሁኔታዎችን ያዘለ አንቀጽ ያካተተ ሕግ አፅድቋል።

ሕጉ የአገሪቱን ዓመታዊ የ2014 በጀት አሜሪካ እርዳታ የምትሰጣቸውን አገሮች እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የገንዘብ ተቋማት የሰብዓዊ መብት ተቋማትና የመሳሰሉትን በጀት ያካተተ ነው።በዚህ ዳጎስ ያለ ሕግ ላይ በአንቀጽ 70ሺ42 ገፅ 1ሺ294 ላይ የአሜሪካ መንግስት ለኢትዮጵያ የሚሰጠውን ወታደራዊና የልማት እርዳታዎች የሚመለከት ሆኖ እናገኘዋለን። ከፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ከምክትሉ ጆ ባይደን ከአሜሪካ የህግ አውጪ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጆን ቦህነር ቀጥሎ የሴኔቱ ፕሬዚዳንት በስልጣን ተዋረዳቸው ደግሞ አራተኛው ሰው በመባል የሚታወቁት ከፍተኛ ሴናተርና ዴሞክራቱ ፓትሪክ ሌሂ አማካኝነት አንቀፁ እንዲካተት መደረጉ የሚገለፀው ይኸው ህግ እንደ ኦክላንድ ኢንስቲትዩት የማህበረሰብ ተቋም የፖሊሲ ዳይሬክተር ፍሬድሪክ ሙሶ ታሪካዊ ህግ ተብሎ እየተወደሰ ይገኛል።

ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ መንግስትን አስተዳደር የሚቃወሙትና ኤችአር 2003 በመባል የሚታወቀውን ህግ ያረቀቁት ሴናተሮች ዶናልድ ሜይና ክሪስ ስሚዝ በጉዳዩ ላይ ምንም አይነት እውቀት ሳይኖራቸው በአሜሪካ የሚገኙ የኢትዮጵያ መንግስት አግባቢዎች/ሎቢስት እንዲሁም በአምባሳደር ግርማ ብሩ የሚመራው በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ህግ አነፍናፊ አታሼዎች እውቅና በላይ ሳይታሰብ በድንገት ህግ ሆኖ የወጣው ይኸው አንቀጽ የሁለቱን አገራት መንግስታት ግንኙነት ሊፈታተነው እንደሚችልም ከወዲሁ ተገምቷል።

የህጉ አንቀጽ እንደሚያስገድደው የአሜሪካ መንግስት ለኢትዮጵያ የሚሰጠው እርዳታ በትክክል ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የአሜሪካ ውጭ ጉዳይና የገንዘብ ሚኒስትሮቹ ማረጋገጥ አለባቸው።በጀቱ በስራ ላይ ከመዋሉም በተጨማሪ በጀቱን በቀጣይ ለመልቀቅ 1ኛ/ ገለልተኛ ዳኝነት መኖሩን ማረጋገጥ ወይም ወደ ገለልተኛ ዳኝነት ለማምራት ጥረት እንደሚደረግ ውጤታማ እቅዶች በስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ 2ኛ/ የኢትዮጵያ መንግስት የመናገር ራስን የመግለፅ መብት መጠበቁን ሰላማዊ ስብሰባዎች ማካሄድን በእምነት ተቋማት ላይ ተፅዕኖ ያለማ ድረግ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በነፃነት እንዲሰሩ ዜጎች ከህግ ውጭ የማይታሰሩና ማዋከብ የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ 3ኛ/ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል የመጎብኘት ዕድል እንዳይነፈጉ፤በክልል የሰብዓዊ መብት ጥሰት በፈፀሙ የፖሊስና የመከላከያ ሃይሎች ላይ ክስ እንዲመሰረት 4ኛ/በኦሞ ሸለቆና በጋምቤላ ክልል አካባቢዎች በሰፈራ ስም ዜጎች ከመሬታቸው እንዳይፈናቀሉና እንዳይሰደዱ ማረጋገጥ 5ኛ/ከአሜሪካ ህዝብ ቀረጥ ከፋዮች ተሰብስቦ ለኢትዮጵያ እርዳታ የሚውለው ገንዘብ የዜጎቹን ህይወት የሚያሻሽል እንጂ ድህነቱን የሚያባብስ እንዳይሆን ሁለቱም ሚኒስትሮች አረጋግጠው ለበጀት ኮሚቴው ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው የህጉ አንቀጽ ያስገድዳል።በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርዓቱ መሻሻልና የመልካም አስተዳደር መስፈንን በቅድመ ሁኔታነት የሚያስቀምጥ ህግ ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ ቀደም በሚሰጡ እርዳታዎች ላይ እርዳታውን ከመስጠት የዘለለ የቁጥጥር ነገር ስለማይደረግ ከፍተኛ ንብረትና ሃብት ተመዝብሯል የሚል ክስ የሚደመጥበት የኢትዮጵያ መንግስት ከአሁን በሁዋላ እያንዳንዷ ዶላር የት እንደዋለች የማሳመን ሃላፊነት ተጥሎበታል።



**ሴናተር ዶክተር ፓትሪክ ሌሂ/ፎቶ ከግላቸው ድረ-ገጽ**

ሴናተር ሌሂ በተደጋጋሚ ጊዜያት በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊና የዴሞክራሲ መብቶች አያያዝ ላይ የተለያዩ ሪፖርቶችን አቅርበዋል።በተለይ በቅንጅት አመራሮችና በእስክንድር ነጋ መታሰር በሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ሰፊ ንግግር አድርገዋል።እኚህ ሰው ታዲያ ያላቸውን የካበተ ልምድና የ40 ዓመት የሴናተርነት አገልግሎታቸውን በመጠቀም አንቀፁ እንዲካተት በማድረጋቸው በሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች በማህበረሰብ ተቋማት በኢትዮጵያውያን አክቲቪስቶችና በዲያስፖራ በሚገኙ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ምሁራን ምስጋና እየተቸራቸው ይገኛል።

## የህጉ አንደምታ

ህጉ የዜጎች መብት እስካልተጣሰ ድረስ እርዳታ መሰጠቱን አይቃወምም። ድንጋጌው በሐምሌ 2013 ተጠንስሶ በቅርቡ ህግ ሆኖ የወጣው ይኸው አስገዳጅ አንቀጽ ለኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ የቤት ስራ የሰጠ ሆኗል።ተጠያቂነት አስቀምጧል።ይሄ ካልተፈፀመ እርዳታውን በቀጣይ ዓመት ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ደግሞ በየዓመቱ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ከአሜሪካ መንግስት በእርዳታ የምታገኝ በመሆኑ ይህን ርዳታ ለማግኘት ቅድመ ሁኔታዎቹን ቢያንስ በአጭር ጊዜ የማሟላት ግዴታ ይኖርበታል።እንዲህ በቀላሉ ከማንም የማታገኘው እርዳታ ስለሆነም የኢትዮጵያን መንግስት ቢያንስ የተወሰነ የፖሊሲ ማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ያስገድደዋል። በቅርቡ አቶ በረከት ስምኦን እንዳሉት ገበሬው ተኛ ስንለው ይተኛል ሩጥ ስንለው ይሮጣል ምንም ብናደርገው ተሸክሞን ይዞራል ያሉት ነገር የሚሆን አልመሰለኝም።ህዝቡን እንደፈለክ በተለይ በእኛ ገንዘብ ልታሽከረክር ከአሁን በሁዋላ አትችልም እየተባለ ነውና።ያው ገበሬውም ቢሆን የሚያገኘው የእርዳታ እህል በአብዛኛው የሚገኘው ከዚቹ ከአሜሪካ አይደል?ስለዚህ ቀደም ብሎ ነበር እንጂ አሁን እንኳን የአሜሪካ መንገድ የካሮትና የዱላው አማራጭ ይመስላል።

## የኦባማ አስተዳደር

የሕጉን አንቀጽ የኦባማ አስተዳደር እንዴት ሊያልፈው ቻለ?የሚለው ጉዳይ በአሁኑ ወቅት በጣም አነጋጋሪ ሆኗል።የአብዛኞቹ ምሁራን ሃሳብ ወደ አንድ ያዘነበለ ነው።እሱም አንቀጹ የተካተተው በአንድ በሺዎች በሚቆጠሩ ገፆች ባሉት የበጀት ህግ ውስጥ በመሆኑና በዴሞክራቶቹና በሪፐብሊካኖቹ መካከል በርካታ አጨቃጫቂ አንቀፆች የነበሩ በመሆናቸው ብዙ ትኩረት ሳይሰጡበት ሾልኮ አምልጧል የሚል ነው።ምክንያቱም የኦባማ አስተዳደር ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ያለው ጥብቅ ግንኙነት በዚህ ሁኔታ እንዲሻክር አይፈልግምና።የህጉን አንቀጽ አስተዳደሩ አውቆት ቢሆን ኖሮ ህግ ሆኖ እንዳይወጣ ያደርገው እንደነበርም መገመት ተገቢ ነው።የአሜሪካ መንግስት አቋሙ ምን እንደሆነ እስካሁን በይፋ የገለፀው ነገር የለም።ለህጉ ከመገዛት ግን ሌላ የተሻለ አማራጭ አይኖረውም።መንግስቱ ለፓርላማው ተገዥ ነውና።

## የህጉ ተግባራዊነት

የህጉ ተግባራዊነት የግድ ይላል።ምክንያቱም በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አንቀጹ በህጉ ተካቶ ፀድቋል።ይህህ የህግ አንቀጽ ይዘውም ማንኛቸውም የኮንግረንሱ አባላት ይመለከተኛል የሚልም ዜጋና ተቋም የአሜሪካ ባለስልጣናትን ፍርድ ቤት አቁሞ ለተግባራዊነቱ ሊሞግታቸው ይችላልና።የኦባማ አስተዳደር በዚህ ሁኔታ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ያለው ግንኙነት እንዲሻክር ባይፈልግም የፓርላማውን ውሳኔ የማስፈፀም ሃላፊነት ስላለበት አዎንታዊ ጫና ሊያሳድር ይችላል።

## የኢትዮጵያ መንግስት ምላሽ/ስጋት

በእርግጥ በጉዳዩ ላይ መንግስት እስካሁን ያለው ነገር የለም።ከነበረው ሪከርዱ መረዳት እንደሚቻለው ግን የአሜሪካ መንግስት የሚሰጠው እርዳታ አነስተኛ ነው።ከአሜሪካ የምናገኘውን እርዳታ ጨምራ ቻይና ትሰጠናለች።መንገዳቸውን ጨርቅ ያድርግላቸው።የሚሉ ምላሾች እንደሚሰጡ ይጠበቃል።

ነፍሳቸውን ይማርና የቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ የቀታ ስርጭት በሚተላለፍበት በአንድ የፓርላማ ስብሰባ ላይ በሶማሊያ የተካሄደውን ጦርነት አስመልክተው ስለ አሜሪካ የገንዘብ ድጋፍ ተጠይቀው አሜሪካ ኮንዶም ነው የምትረዳን በኮንዶም ነው ወይ ሶማሊያ የምንዋጋው?ብለው መናገራቸውን አስታውሳለሁ።ከዚህ በመነሳት የራዕያቸው ተረካቢዎችም ቃላት ለዋውጠው ወይ ይህንኑ ወርሰው ሊናገሩ ይችላሉ።አንዳንዶቹም አሜሪካ ሉዓላዊነታችንን ትነካለች ስለዚህ እርዳታው ይቅርብን ሊሉም ይችላሉ።የኦባማ አስተዳደርም አንቀጹ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ እንዳይሆን የመከላከል በአንዳንድ ጉዳዮችም ላይ የተለየ አቋም ሊይዝ ይችላል።

በእኔ የህግ እውቀት ከሆነ ይህ ህግ ሆኖ የጸደቀው አንቀጽ ራሱን ችሎ ያልወጣ በመሆኑና በበጀት ህጉ ውስጥ ተካቶ በመፅደቁ ብሎም ከህጉ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው የ2014 የዩናይትድ ስቴትስ የበጀት ህግ በመሆኑ የኦባማ አስተዳደር ካላመነበት ከአንድ ዓመት የዘለለ እድሜ ስለማይኖረው የተደረጉት ጥረቶች በድል ተጠናቀዋል/ mission accomplished/ ማለት አያስችልም።

## መልካም እድሎች

የኢትዮጵያ መንግስት የአሜሪካ እርዳታ ይቅርብኝ ቻይና አለችልኝ የሚል ምላሽ መስጠት አያዋጣውም።ምክንያቱም ቻይና የኢትዮጵያ መንግስት ህዝቡን ረገጠም በህዝቡ ተረገጠም ጉዳዬ ብላ አትከታተልም። ንግዷን እስካጧጧፈች ድረስ መስጠት የምትፈልገውን ትሰጣለች። ስለዚህ የአሜሪካ እርዳታ መቅረት ከፍተኛ ችግር እንደሚፈጥር በመረዳት ወደአላስፈላጊ ግጭት እንዳይሄድ በመፍራት የኢትዮጵያ መንግስት በአፈቀላጤዎቹ/ሎቢስት ጭምር ሳይቀር ለመደራደር የሚገደድበት ሁኔታ ይፈጠር ይሆናል።ብሎም የአውሮፓ ህብረት ከአሜሪካ በላይ ለኢትዮጵያ ገንዘብ የሚረዳ ተቋም ነውና እሱም የአሜሪካ መንግስትን አቋም ደግፎ ተመሳሳይ ውሳኔ ላይ ከደረሰ የኢትዮጵያ መንግስት እጅግ ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ ነው የሚገባው።ስለዚህ ቢያንስ ቢያንስ ለፕሮፓጋንዳ እምቢኝ ዘራፍ ቢልም ቀስ በቀስ ጉዳዩን እኛም በትራንስፎርሜሽኑ እቅዳችን ይዘነው ነበር በማለት ፖሊሲዎቹን የማስተካከል እርምጃ እንደሚወስድ መገመት ይቻላል።



## መደምደሚያ

ያም ሆነ ይህ ይሄ ሸንቋጭ ህግ በኮንግረንሱ ፀድቆ ወጥቷል።አሜሪካም ከመግለጫ ያለፈ እርምጃ እንድትወስድ ሲጨቀጭቋት ለነበሩት አካላት መጠነኛ እፎይታ እንዲያገኙ አድርጋለች።እሰጣ ገባው የሚወሰነው ግን በዋነኝነት የኢትዮጵያ መንግስት በሚይዘው አቋም ላይ ይሆናል።

በአሜሪካ ኮንግረንስ የፀደቀው የህግ አንቀፅ እመራዋለሁ አስተዳድረዋለሁ አገሬ ነው ዜጋዬ ነው ለሚል ስርዓት አጋዥ እንጂ ፀሩ የሚሆንበት ሁኔታ ስለማይኖር የኢትዮጵያ መንግስት የተጣለበትን ሃላፊነት ተረክቦ ለህዝቡም ለአገሪቱም የሚበጀውን ይሄን ውሳኔ ያስተግብር!አራት ነጥብ።

# በፕሬስ አፈና ግንባር ቀደም አገር - ኢትዮጵያ

**Yostina Yilma/ Bayreuth**

ኢትዮጵያ ውስጥ የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች ሥራ ላይ ከዋሉ 22 ዓመታት እየተቆጠሩ ነው:: በእነዚህ ዓመታት በበርካታ ውጣ ውረዶች ውስጥ በማለፍ የግሉ ፕሬስ ውጤቶች ጠቃሚ አስተዋጽኦ ማበርከታቸው አይካድም:: አሁንም በጎርባጣው ጎዳና ላይ እየተጓዙ ናቸው:: በመቶዎች የሚቆጠሩ የፕሬስ ውጤቶች ይቀርቡባቸው የነበሩ ዓመታት አልፈው አሁን ውስን ጋዜጦችና መጽሔቶች ቀርተዋል:: በእነዚህ ዓመታት የግሉ ፕሬስ ፈተናዎች በሁለት ምክንያቶች ሥር ሊጠቃለሉ ይችላሉ:: አንደኛው ውጫዊ ሲሆን፣ ሁለተኛው ውስጣዊ ችግር ነው::

የውጭውን ተፅዕኖ ስንፈትሽ ችግሩ ከመንግሥት ይጀምራል:: መንግሥት የፕሬስ ነፃነትን በተመለከተ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመርያዎችን ከማውጣት ባለፈ ለፕሬሱ ዕድገት የሚያደርገው አስተዋጽኦ የለም ማለት ይቻላል:: ሕጎች ሲወጡም በፕሬስ ውስጥ የተሰማሩ ዜጎችን ፍላጎቶች፣ ችግሮችና ተጨባጭ እውነታዎች ስለማያገናዝቡ ጋዜጠኞችና መንግሥት ሊግባቡ አልቻሉም:: በአንዳንድ ሹማምንት የግሉ ፕሬስ እንደ ጠላት ተደርጎ ይፈረጃል:: በሕገ መንግሥቱ የተሰጠው ዕውቅና እየተዘነጋ መረጃ ይከለከላል:: ጋዜጠኞች በረባውና ባልረባው ነገር ይታሰራሉ:: ሕግ እየተጣሰ በሕገወጥ መንገድ ሲንገላቱ ጠያቂም ሆነ ተጠያቂ አካል የለም:: ለስደትም የተዳረጉ ብዙዎች አሉ። በአጠቃላይ የግሉ ፕሬስ ህልውና ላይ ጥላው ካጠላ ሰነባብቷል።

አሁንም ቢሆን አፈናው ተጠናክሮ በመቀጠሉ የመናገር ነፃነቱ ወደ ባርነት ተለውጧል። ስለዚህ በስደት አገር ሆነን ለታፈኑት ውድ ወገኖቻችን ልንተነፍስላቸው ይገባል።የፕሬስ ነፃነት ይከበር! ቸር እንሰንብት ።

# ሉዓላዊነታችን ይከበር

**Helen Tesfay/Gießen**

የአንድ አገር ህዝብ የማንነትና የክብር መገለጫ የሆነው መሬት በስርዓት ካልተጠበቀ በሃገር መከበር በሃገር መኩራት እንዲሁም ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ አፍን ሞልቶ መናገርና ያሳጣል።ዛሬ እኛ ኢትዮጵያ እያልን የምንጠራት የምንኖርባት አገሬ ኩራቴ ብለን ያዜምንባት በተለያየ መንገድ ፍቅር እየሰጠናት በእናት አምሳያ የምንጠራትን በተፈጥሮ ውበት የታደለች የቱባ ባህል ባለቤት በዓለም አደባባይ ከፍ ብላ የምትታይ የማናፍርባት ኢትዮጵያን ሉዓላዊነቷን ድንበሯን ያስከበሩልንን አባቶቻችን አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍስሰው ነው።

የኢትዮጵያ መሬት የአባቶቻችን የደም አሻራ ያረፈበት ነው።ይህንን አደራ ትውልዱ ሊጠብቀውና ታሪኩን የማስቀጠል ሃላፊነት አለበት።
መሬታችን ለሱዳን አሳልፎ መስጠት ከባድ ወንጀልና ክህደት ነው።ስለሆነም ኢትዮጵያውያን ቁጣቸውን በአገርና በውጭ በመግለፅ ላይ ናቸው።ይህ ትግል የህልውና ጉዳይ ነው።የአገሬን መሬት ለሱዳን ለመስጠት ወያኔ በጓዳ መዋዋሉን አጥብቄ እቃወማለሁ።

አባቶቻችን ከደሙለትና ከተሰውለት ድንበር ስንዝር ታክልም መሬት በማንኛውም ምክንያት ለሌላ አገር ተላልፎ እንዲሰጥ አልፈቅድም።በተጨማሪም በሉዓላዊ ግዛታችን ላይ የሚደረግ ማንኛውንም ስውር ሴራ ከወዲሁ ልንገታውና በአንድነት ቆመን ታሪካችንን በማደስ ማንነታችንን ልናሳያቸው ይገባል። ይህ ስውር ደባ በአስቸኳይ እንዲቆም በሚደረጉ ትግሎች ላይ የበኩሌን አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ።እናም ወያኔ በአስቸኳይ ከድርጊቱ እንዲታቀብ እጠይቃለሁ።

# አንድን ህዝብ ዒላማ ማድረግ በሽታ ነው።

**Tigist Alebachew/ Bayrueth**

ህወሓት (ተሓህት) የአማራን ህዝብ ዒላማ አድርጎ ሲነሳ፣ ሌሎች የህወሓት ተቃዋሚዎች ደግሞ በህወሓት ምክንያት የትግራይን ህዝብ ዒላማ ሲያደርጉ ዉጤቱ ምን ይሆናል? አንድን ህዝብ ከሌላ ህዝብ ጋር የማጣላት ስትራተጂ የፖለቲካ ዕብደት ነው። ህዝብና ገዢው መደብ አለመለየየት (አንድ እንደሆኑ አድርጎ ማሰብ) የፖለቲካ እውቀት ማነስ ዉጤት ነው። ስርዓቱን መቃወምና መታገል እየተቻለ ህዝብን ዒላማ አድርጎ በህዝቦች ላይ መተማመን እንዳይኖር መትጋትና በህዝቦች መካከል ጥላቻ እንዲነግስ መስራት ጠባብነት ነው።

አንድ ህዝብ የበላይነት ሊይዝ አይችልም። አንድቡድን ግን በአንድ ህዝብ ስም በመነገድ ሌሎችን ሊበድል ይችላል። የሰው የበላይነት (በህዝቦች ላይ) ሊተገበር ይችላል። ህ ዝብ እንደ ህዝብ ግን ሌላውን ህዝብ ሊበድል አይችልም። ህወሓት የትግራይን ህዝብ እንደሚወክል ይነግረናል። የትግራይን ህዝብ እወክላለሁ እያለ ሌሎች ህዝቦች (የትግራይን ጨምሮ) ይበድላል። ሌሎች ህዝቦች (ከትግራይ ዉጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን) ደግሞ በህወሓት ስርዓት ሲበደሉ በትግራይ ህዝብ የተበደሉ አድርገው ያስባሉ። ግን ስህተት ነው። መታረም አለበት።

የትግራይ ህዝብ ለራሱ በህወሓት አገዛዝ የሚበደል ነውና።የትግራይ የበላይነት" የሚባለው የህወሓት በሽታ እስካሁን ፈውስ አላገኘም። በመርህ ደረጃ ህዝብን ዒላማ አድርጎ ህዝብን ለመታገል መነሳት ስህተት ነው ብያለሁ። በፖለቲካ ህዝብ ዒላማ አይደረግም። ምክንያቱም የፖለቲካ ዓላማ ህዝብን ማገልገል እንጂ ህዝብን መጨቆን አይደለም። ስለዚህ ህዝብን የመበደል ዓላማ መያዝም መተግበርም የህሊና ወንጀል ነው። ህወሓቶች ይህን በሽታ ("የአማራ የበላይነት" መፈክር) አልተዋቸውም። አሁንም "ፀረ አማራ" እንቅስቃሴዎች አሉ። የህወሓት የአሁኑ ስትራተጂ "እኛ ከስልጣን የምንወርድ ከሆነ ከአማራ ጋር አብረን አንቀጥልም" የሚል ገንጣይ አስተሳሰብ እያራመዱ ይገኛሉ። "እኔ ከሌለሁ ሣር አይብቀል ..." ዓይነት ስትራተጂ መሆኑ ነው። በጣም የሚገርመው ነገር ፀረ ብአዴንም መነሳታቸው ነው።

ግን ይህን "አማራ" የሚባል ህዝብ መቼ ይሆን የበላይነት ይዞ ሌሎች ህዝቦችን የበደለው? አንድን ህዝብ እንዴት ሌላውን ህዝብ ይበድላል? ህዝብ ህዝብን ሊበድል አይችልም። ምክንያቱም አንድን ህዝብ ሌላውን ህዝብ መበደል ከጀመረ (ከቻለ) ህዝብ መሆኑ ቀርቶ ገዢ መደብ (elite) ሁኖዋል ማለት ነው። ገዢ መደብ ከሆነ ደግሞ ህዝብ አይደለም። ገዢ መደብ ስርዓት ነው። ህዝብና ስርዓት ደግሞ ይለያያሉ።ስለዚህ ገዢዎች የሚወክሉት የፈጠሩትን ስርዓት እንጂ የመጡበትን ብሄር አይደለም።

# የአገራችንን ድንበር አናስደፍርም!

**Tigist Kurabachew/ Nürnberg**

ከሰሞኑ ወቅታዊ የመነጋገሪያ አጀንዳ የሆነው የኢትዮ-ሱዳን የድንበር ጉዳይ ነው።ሱዳኖች ወያኔዎችን አሳምነው ቀላል

የማይባል መሬት ለሱዳኖች ሲለግሷቸው መሆኑም እየተሰማ ነው። እንደ ሱዳን ትሪቡን የመሳሰሉ ሱዳን በቀል የመረጃ መረቦች ጉዳዩን በደስታ እያንበለበሉት ይገኛሉ።

የሱዳን ባለስልጣናትም ከኢትዮጵያው ገዢ መንግስት ጋር አደረግነው በሚሉት የድንበር ድርድር ደስተኛ መሆናቸውን እየገለፁ ነው።መላው ኢትዮጵያዊ ግን የአገር ድንበርን የሚያህል ጉዳይ በሚስጥር ድርድር ለመጨረስ ማኮብኮቡ አግራሞትን ፈጥሮብኛል።

ከኤርትራ ጋር ያን ያህል ደም ከፈሰሰ በሁዋላ ባድመን ቢወስዷትም ባይወስዷትም ዘላቂው ነገር የህዝቦች ግንኙነትን ማጠናከር ነው በሚል ሽፋን ዳር ዳር ማለት የጀመረው ገዢያችን አሁን ደግሞ በድብቅ ለሱዳን መሬት ቁርሶ ለመስጠት መዘጋጀቱ ምን ያህል ለህዝቡ ንቀት እንዳለው በቂ ማስረጃ ስለሆነ የዓለም መንግስታት በሁዋላ ጦርነት እንዳይነሳ አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርጉ ይገባል።ኢትዮጵያውያንም ድምፃችንን ከፍ አድርገን ልናሰማ ይገባል። የአገራችንን ድንበር አናስደፍርም!

# ዝምታችን ይብቃ!

**Firezewed Berhanu/ Fulda**

ለብሔርና ብሔረሰቦች መብትና እኩልነት ቆምያለሁ እያለ የሚደሰኩረው የወያኔ ስርዓት ከ3ሺ ዓመታት በላይ ህዝቦቿ በአንድነት በመከባበርና በሰላም ይኖሩባት የነበረችውን አገር በከፍተኛ የኑሮ ውድነት ጫና ብሔር ብሔረሰቦችን በመከፋፈልና በማጋጨት ገበሬውን የእርሻ መሬቱን በመንጠቅ ለተለያዩ የባዕድ አገር ባለሃብቶች በሙስና እየለገሰ ገበሬውን ለረሃብ እና ለስደት እየዳረገ ይገኛል።

ለህዝቦች መብትና ጥቅም መከበር የሚታገለውን ወጣቱን በማሰር በማሰቃየት ሰዶ በማሳደድ ከትምህርት ገበታ በማባረር በመግደል ጭምር እያሰቃየው ነው።የመንግስትና የግል ሰራተኞችን ደግሞ የገዢው ፓርቲ የግዴታ አባል እንዲሆኑ ካልሆኑ ደግሞ ከስራ እስከማባረር የሚደርስ እርምጃ እየተወሰደ ነው።

በመንግስት መዋቅሮች በተንሰራፋው ሙስና ገዢዎቻችን የራሳቸውን ጥቅም ብቻ በማሳደድ አገሪቱን አዘቅት ከተዋታል።እናስ የኛ ዝምታ እስከመቼ ይሆን? ለዚህ መፍትሄ አገሩን ወገኑን ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የወያኔን አክርካሪ ለመስበርና ወደመጣበት ለመመለስ ብሎም ለኢትዮጵያ ትንሳኤ እየታገለ ካለው የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ጋር ሁሉም መሰለፍ አለበት።ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር !

# የ ሚ ያ ስ ፈ ል ገ ን ዴሞክራሲ ብቻ ነው!

**Betewedag Adnew /Bayreuth**

በትግርኛ "ካብ ጭርሖታት ህወሓት 1969 ዓም: ሃፀይነት፣ መስፍንነትን ናይ አምሓራ ዕብለላን ዓነውቲ እዮም!" ይላል። ግርማይ ገብሩ አልተሳሳተም። ከህወሓቶች ጋር የማልስማማበት ግን ነጥብ አለኝ፡ "አፄነት፣ መስፍንነት እርግጥ ነው። እኔም አፄነትና መስፍንነትን እንደ ስርዓት አልቀበልም። ምክንያቱም አፄነትና መስፍንነት (እንደ ስርዓት) ላሁኗ ኢትዮጵያ አይመጥኑም። የአፄነትና መስፍንነት ስርዓት በኢትዮጵያ ታሪክ እዚ ግባ የሚባል ለውጥ አላመጣም። ስለዚህ እኛ የሚያስፈልገን ዘመናዊ (ከዘመኑ ንቃተ ህሊናችን ጋር አብሮ የሚሄድ) የህዝብ አስተዳደር (ዴሞክራሲ) እንጂ ንጉስነት (የሰው ገዢነት) አይደለም። የምንፈልገው የሕግ የበላይነት እንጂ የንጉስ የበላይነት አይደለም።

ግን አፄነትና መስፍንነት እንደ ስርዓት ባልቀበለውም የንጉሳውያን ቤተሰቦችና መሳፍንቶች መጥፋት አለባቸው ብዬ ግን አላምንም። እኔ ብሆን እነኚህ የንጉስ ቤተሰቦችና መሳፍንት ቁልፍ የመንግስት ስልጣን እፈቅድላቸው ነበር። ምክንያቱም እንደማንኛውም ሰው ዜጎች ናቸው፤ ለሀገራቸው በተቻላቸው መጠን አስተዋፅዖ አድርገዋል።

ህወሓት ግን በመፈክር ደረጃ በጠላትነት ፈረጃቸው። በተግባርም አጠፋቸው፣ ገደላቸው። በንጉሳዊ ቤተሰብና መስፍንነት ዝንባሌዎች ሰበብ ብዙ የተምቤን፣ ዓጋመ፣ እንደርታ፣ ዓድዋ፣ ሽረ፣ አክሱም ወዘተ መሳፍንቶች እንዲጠፉ ተደረገ። 'ትግራይ ከመሳፍንቶች ነፃ ወጣች' ተባለ። እውነታው ግን 'ትግራይ ተገደለች' መባል ነበረበት። መሳፍንቶች ከስልጣን ማውረድ እየተቻለ መግደል ምን አመጣው (ህወሐሌላውና መሰረታዊ የህወሓት ችግር "የአማራ የበላይነት ይውደም!" የሚል መፈክር ነው። እኔም ብሆን የማንም ሰው ወይ ብሄር ወይ ሌላ አካል የበላይነት አልቀበለም። የቴድሮስ ወይ ዮሃንስ ወይ ምኒሊክ ወይ ኃይለስላሴ ወይ መንግስቱ ወይ መለስ ወይ ኃይለማርያም ወይ አማራ ህዝብ ወይ ትግራይ ህዝብ ወይ ኦሮሞ ህዝብ ወይ ሌላ ... የበላይነት አልቀበልም። እኔ የምቀበለው የበላይነት 'የሕግ የበላይነት' ብቻ ነው። የሌላ የማንም የበላይነት አልቀበልም።ገዢዎችን ከስልጣን ማውረድ እየተቻለ መግደል ለምን ያስፈልጋል)?

የአማራ ህዝብ እንደ ማንኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በኢትዮጵያ ገዢዎች ሲሰቃይ የነበረ ነው። ባልበላበት በልተሃል፣ ባልገዛበት ገዝተሃል ሲባል ይገርማል፤ ልክ እንደ ትግራይ ህዝብ። የትግራይ ህዝብ ሳይበላ በልተሃል፣ ሳይገዛ ገዝተሃል ይባላል፤ ህወሓት በበላው፣ ህወሓት በገዛው። ህወሓት ትግርኛ ተናጋሪ ስለሆነ ከትግራይ ህዝብ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም (በፖለቲካ መልኩ)። ያለፉ ገዢዎች አማርኛ ስለሚናገሩ ከአማራ ህዝብ ጋር የሚያገናኛቸው ነገር የለም። ህዝብ ሌላ ገዢ ሌላ።

# የኢትዮጵያ ድንበሮች በደምና አጥንት የተገነቡ ናቸው

**Betelehem Gedle/HOF**

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሃብቷ የታደለች ፣መልካም የአየር ፀባይ ያላት፣ህዝቦቿ የራሳችን አኩሪባህልና ወግያለን፣የራሳችን መልካም መልክዓ ምድራዊና አሰፋፈር ያለን በጋራ ተሳስረን አብረን የኖርንባትና የምንኖርባት በየትኛውም ዘመን ሉአላዊነቷ ያልተደፈረ ለአፍሪካ ተምሳሌት የሆነች ሀገር ናት። በተለያየ ወቅት የተፈጥሮ ሃብቷን ለመቀራመትና ሉአላዊነቷን ለመዳፈር የሞከሩ ሃገራት ሁሉ፣በውድ ልጆቿ የተባበረ ክንድ አይቀጡ ቅጣት ተቀጥተው ኢትዮጵያን ዳግም እንዳይመኟት የተባባሩበትና የኢትዮጵያን አይበገሬነት በአፍሪካም ሆነ በአለም መድረክ ያስመሰከረች፣ አንድነቷንና ሉዓላዊነቷን ጠብቃ በማቆየት በአለም ታሪካዊ ስፍራ ያላት ናት።

በአሁኑ ሰዓት ኢህአዴግ/ህወሃት ለግልና ለግዚያዊ የፖለቲካ ጥቅም ሲል የኢትዮጵያን አንድነት በማዳብዘዝ እንሆ በእኛ ዘመን ለዘመናትተደፍሮ የማያውቀውን የኢትዮጵያን ሉአላዊነት በመጋፋት የኢትዮጵያ የሉአላዊነት ባለቤት የሆኑት ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሳይወያዩበትና ሳያፀድቁት በጓሮ በር የኢትዮጵያን መሬት ለባዕድ ሃገር/ሱዳን ቁርሶ ለመስጠት ሽርጉዱን ተያይዞታል።

ከአመታት በፊት በምዕራቡ የሃገራችን ክፍል /ድንበር በኩል/ በመሸራረፍ ለም የሰሊጥ ምርት የሚሰጥ መሬት ለሱዳን ሲሰጥ ዝም በማለታችን እንሆ ዛሬ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት የሚጋፋ ፣ የኢትዮጵያን ቅርጽ የሚያጠፋ ረጅም ርዝመት ያለው ለም መሬት ለሱዳን ለመስጠት ዝግጅቱ መጠናቀቁን ሰማን።

ዛሬ ላይ ሆነን ይህንን መሰሪ ተግባር አንድነታችንን አጠናክረን መግታት ካልቻልን ነገ ደግሞ በሌላኛው የኢትዮጵያ ጫፍ በኩል የኢትዮጵያ መሬት ተቆርሶ

ለሌሎች አጎራባች ሀገራት ላይሰጥ ምን ዋስትና አለን?

በመሆኑም የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ሉአላዊነት በመጋፋት ለም መሬታችንን ለሱዳን አሳልፎ የሚሰጠውን ስምምነት አገር ወዳድ የሆንን ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በጋራ በመንቀሳቀስ በደምና በአጥንት መስዋዕትነት ተከብሮ የቆየ የሃገራችንን ዳር ድንበር ለባዕድ አሳልፈን አንሰጥም! በሚል መርህ ተግባብተን ይህንን እኩይ ተግባር ለማስቆም ግዜ ሳንወስድ በያለንበት ፈጥነን መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል።

# ራሳችንን እንመርምር

**Mekdes Habtamu/Würzburg**

በደርግ ዘመን ኮሚቴ በዝቷል ይቀነስ ሲባል ኮሚቴ የሚቀንስ ሌላ ኮሚቴ እንዲቋቋም ተወሰነ እየተባለ የሚተረተው ቀልድ ቀልድ ብቻ አይደለም፡፡ የተሰጠው መፍትሔ ችግሩን የሚጨምር እንጂ የሚፈታ አለመሆኑን የሚያሳይም ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ፈተና ማኅበራት ካልነበሩበት ዘመን ይልቅ በበዙበት ዘመን ብሷል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን ቦታ የያዙት በማኅበራት ዘመን ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን መድረክ ሐውልት መቆም የጀመረው፣ የፎቶ ፖስተር በዐውደ ምሕረት የተሰቀለው፣ የቤተ ክርስቲያን ያልሆነ ትምህርት በዐውደ ምሕረት መሰጠት የጀመረው፣ ቅዱስ ሲኖዶስ ተዳክሞ ግለሰቦች ቦታውን መያዝ የጀመሩት በማኅበራት ዘመን ነው፡፡

አሁንም የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች ለመፍታት ተብለው የመጡ መፍትሔዎች እና የተቋቋሙ አካላት በራሳቸው መታየት አለባቸው፡፡ በርግጥ እነዚህ መንገዶች እና አካላት ችግር ጨምረዋል ወይስ መፍትሔ አምጥተዋል? እነርሱ ራሳቸውም ራሳቸውን ማየት አለባቸው፡፡ ምንድን ነው ያመጣነው ለውጥ? ካለመ ኖራችን መኖራችን ምን ይጠቅማል? የቆምነው በትክክለኛው መንገድ ላይ ነውን? ብለን መጠየቅ አለ ብን፡፡ ከላይ የተጠቀስነው አካላት ራሳችንን እንመርምር፣ በተለይም አመራሮቹ ወይም ዋና ዋናዎቹ አሁን የምንሄድበትን መንገድ ከወቅቱ ችግሮች እና ተግዳሮቶች አንፃር እንመዝነው፤ ከዚያም ችግር ሳይሆን መፍትሔ የሚያደርገንን አቅጣጫ እንትለም፡፡ ያለበለዚያ ግን ምንን ምን ቢመራው ሁለቱም ወደ ገደል ይሄዳሉ የተባለው ይፈጸምብናል፡፡

# መሬት ቆርሶ መሸጥ እድገት ወይስ ውድቀት?

**Fissha Tsion Hailegeberile/ Kronach**

የተከበራችሁ ውድ አንባብያን እንደሚታወቀው ስለ አገራችን ኢትዮጵያ ስናነሳ ሀገራችን መቼም በአሁኑ ወቅት ከምን ደረጃ ላይ እንዳለች ሁላችንም የሃገር ልጆች እናውቃለን።መቼም እያደር የሚሰማው ነገር መግረም ብቻ ሳይሆን እየዘገነነ መጥቷል።እንዲህ ስል ለማጋነን አይደለም።ገዢው የወያኔ መንግስት ሀገራችንን ማስተዳደር ከጀመረ አንስቶ እየፈፀመ ያለው ግፍና በደል ብናነሳው አንጨርሰውም።እናም እኔም እንደ ዜግነቴ ብዙ የሚሰማኝ ነገር አለ።እርሱም ስለሃገሬ ኢትዮጵያ ሳስብ ውስጤ አሮ ከስሷል።ምክን ቱም ወያኔ በአስተዳደር ዘመኑ እየፈፀመ ያለው በደልና ግፍ ህዝቡን ከመከፋፈል ውጭ ያተረፈው አንዳችም ነገር የለም።

በርዕሴ እንደጠቆምኩት የሃገራችንን መሬት የሚቀራመቱ ሃይሎች አገራችንን እጅ ተወርች ጠፍንገዋታል።ወያኔ የአገራችንን መሬት ከግል ይዞታ እስከ እርሻ ቦታ ድረስ በካድሬዎቹ አማካኝነት ነዋሪውን በማፈናቀል ለባለብራሞች እየቸበቸበው ይገኛል።ይባስ ብሎ የስንት አባቶቻችንና እናቶቻችን ደምና አጥንት የተከሰከሰበትን ዳር ድንበራችንን አሳልፎ ለውጭ ሃይል እየሸጠ መሆኑ ሃይ የሚለው እንዳጣ ያመለክታል።

ከሱዳን ጋር በደረሰው ስምምነትም የሑመራን መሬት አሳልፎ ለመስጠት በማኩብኮብ ላይ ይገኛል።በዚህም ምክንያት የአካባቢው ነዋሪዎች ከመንግስት ሃይሎች ጋር እሰጥ አገባ ውስጥ ገብተዋል።የሰው ህይወትም በማለፍ ላይ ይገኛል።እናም ወገኖቼ የወያኔ መንግስት ሃገር ማስተዳደር ወይስ እየቆረሰ መሸጥ ነው የያዘው?ይህንን የዓለም መንግስታት ይወቁልን።እኛም እውነቱን በማጋለጥ ለዳር ድንበራችን ዘብ እንቁም!

# የፍርድ ቤት ባርነት በኢትዮጵያ

**Simret Ayalew Mengesha/ Hochstadt**

ትክክል ነዉ ፍርድ ቤቶች ጋ ትልቅ ችግር አለ። ዋናዉ ችግር ፍርድ ቤቶች ያልበሰሉ ልጆችን ዳኛ ብለው ይቀጥራሉ፡፡ ይህ ደግሞ በሰዎች ሕይወትና ንብረት እንዲሁም ሰብአዊ መብቶቻቸዉ ላይ መቀለድ ነዉ።የዳኝነት ስራ በባሕሪዉ በዕድሜ፡ በስራ ልምድ፤ በትምህርት፤ በባሕሪ ብስለትን ወይም ዕድገትን ይፈልጋል፤፤.የሰዉ ልጅ ደግሞ ፍትሐዊነትን፤ ሚዛናዊነትን ፤እርቆ አስተዋይነትን የሚያዳብረዉ በዕድሜ፤በስራ ልምድ፤ በትምሕርት፤ በባሕሪ እየበሰለ በሄደ ቁጥር ነዉ፡፡ Judgement by its nature requires the highest quality,u could not disregard this fact. That is why፡ almost all countries through out the globe appoint highly qualified Judges. ሌላዉ ትልቁ ችግር ፍርድ ቤት ዉስጥ ሙስና በስፋት አለ፤፤ ሙስና የሚፈጽሙት ዳኞች ብቻ አይደሉም፤፤ ለሎች ከችሎት ስራ ጋር ግኑኝነት ያላቸዉ ብዙ ግለሰቦች ሙስና ይፈጽማሉ ብቻ ሳይሆን ጉቦ ካልተቀበሉ አይሰሩም ወይም ሆን ብለዉ ተንኮል ይሰራሉ።

ሌላዉ ጣልቃ ገብነት ሲሆን ጣልቃ የሚገቡት የመንግስት አስፈጻሚዎችና የየፍርድ ቤቶቹ ሀላፊዎች(የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ) ናቸዉ፡፡ መዝገቡን ከያዘዉ ዳኛ ያለ በቂ ምክንያት ተቀብለዉ ለሌላ ዳኛ ይሰጣሉ፤ በፈለጉት ሁኔታ እንዲወሰንላቸዉ ትዕዛዝ ይሰጣሉ።እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት አንድ ዳኛ ከችሎት የሚነሳዉ በሕግ በተደነገገዉ መሰረት ነዉ። ነገር ግን የያዘዉን መዝገብ የሚቀማበት ወይም ጉዳዩን ሀላፊዉ በሚፈልገዉ ሁኔታ እንዲወስን የሚያዝ ሕግ የለም፡፡ ይህ ድርጊታቸዉ ሕገ መንግስታዊ ስርአቱንና የዳኝነቱን ነጻነት የሚጥስ ከመሆኑም በላይ የሙስና ወንጀል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።ስለዚህ የዳኝነት ባርነት ባለበት አገር በነፃነት መኖር ስለማይታሰብ ለፍትሃዊ ስርዓት ግንባታ የበኩላችንን እንወጣ-መልዕክቴ ነው።

# ሚዛኑን ያልጠበቀ ፍትህ

**Abenezer Ahmed/HOF**

በአንድ አገር ውስጥ ህዝቦች ሰላማዊና የተረጋጋ ኑሮ ለመኖር ከሚያስፈልጉት መሰረታዊ ነገሮች አንዱ ህግ ነው።ህግ ደግሞ ሁሉንም በእኩል የሚያስተዳድርና የበላይ መሆን አለበት።የህግ የበላይነት በሌለበት ሰላም መረጋጋት የሰው ልጆች ሙብት ልማትና ብልጽግና በሰላም ወጥቶ መግባት የማይታሰቡ ናቸው።እነዚህ በሌሉበት ደግሞ በህይወት መኖር ጥያቄ ውስጥ ይገባል።

ስለ አገራችን የፍትህ ስርዓት ስናወራ ሶስቱን መዋቅሮች ማለትም ህግ አውጪ ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈፃሚውን አካል ከህዝቡ የበለጠ ከፍተኛ ሃላፊነትና ሚና አለባቸው።እዚህ ጋር ሊነሳ የሚገባው

ጥያቄ እነዚህ ተቋማት ከጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው ለህግና የህግ የበላይነት ብቻ እየሰሩ ነው ወይ?ብለን ስንጠይቅ መልሱ ለሁላችንም ግልፅ ነው በፍፁም እንዳልሆነ።ህግ አውጪው አካል ማለትም ፓርላማው ህዝብ በትክክል ይወክሉኛል ብሎ ያልመረጣቸውና ወያኔ ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ በተቆጣጠረው መቀመጫ ላይ ተቀምጠው የሚያወጡት ህግ በአብዛኛው አገዛዙን የሚጠቅም ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያግዝ ስለሚሆን ያለክርክርና ተቃውሞ ይፀድቃሉ።

ህግ ተርጓሚው አካል ደግሞ የወያኔ ኢህአዴግ አባላት ሆነው ከህሊናቸው ይልቅ ለቁሳዊ ጥቅም የቆሙ ናቸው።ህግ አስፈፃሚውም ምርመራ ሲያካሂድ ማስረጃን መሰረት አድርጎ ሳይሆን በድብደባና በማሰቃየት ዜጎች ያልፈፀሙትን ወንጀል ፈፅሜያለሁ ብለው እንዲያምኑ የሚያደርግና በዚህ መሰረት አድርገው ተብሎ እየታዘዘ የሚሰራ ስለመሆኑ ሁላችንም የምናውቀው ነው።

በአጠቃላይ በአገራችን ውስጥ ህግ የፖለቲካ ማስፈፀሚያ በመሆኑ ምክንያት ዩህግ የበላይነት አይከበርም።ለዚህም ነው ሰላም ዴሞክራሲ ሰብዓዊ መብት የሌሉትና እንዲሁም ሙስና አድሎአዊነት ዘረፋ ቤተሰባዊ ስልጣንና በማንነት መዳኘት እየተንፀባረቀ ያለው።በአገራችን የተሻለ የፍትህ ስርዓት እንዲኖር ወያኔ ኢህአዴግ ሶስቱን መዋቅሮች የፖለቲካ መሳሪያ ከማድረግ መቆጠብ አለበት።እጁን ከነዚህ ተቋማት ውስጥ አውጥቶ ለህዝብና ለህግ ብቻ ተገዢ እንዲሆኑና በነፃነት ህግን መሰረት አድርገው ማንኛውም የአገሪቱ ዜጋ በህግ ፊት እኩል መሆኑን የሚያሳይ ስራ እንዲሰሩ አቅም ሊኖራቸው ይገባል።በሃይል በጉልበትና በማስመሰል መኖር ይብቃን።

# ለህሊና ማደር

**Yared Abebe/Würzburg**

በወያኔ ስርዓት መላው የአገሪቱ ህዝብ በጣም አስቸጋሪ ኑሮ ሁኔታን መቋቋም አቅቶት የልቡን እንኳን ለመናገር ሁሉም እርስ በርሱ እንዳይተማመን በብሔር በመከፋፈል ወያኔም የሾማቸው ሹመኞች ልክ ወንበሩን ሲይዙ ህሊናቸውን ረስተውት ለሆዳቸው ማደር በጀመሩበት ሰዓት እውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግራ በተጋባበት ሁኔታ አሁንም ህዝቡ ተስፋ ባለመቁረጥ ከነገ ዛሬ የተሻለ መሪ ይመጣል ብሎ ቢጠብቅም የስርዓቱ የደህንነት ሃይሎች ግን በየመንደሩ እየገቡ የስለላ መረባቸውን ዘርግተው ሊያስፈራሩ እየሞከሩ ነው።

ህዝባችን የቻለውና አቅሙ ያለው ቤተሰቡንና የሚያፈቅራት አገሩን ትቶ ለስደት በመዳረግ ለአገሪቱ የተሻለ ነገር ያመጣል ብሎ ያሰበውን ሁሉ በመሰብሰብ የህዝቡ ችግር ችግራቸው የሆኑ ምሁራንን በማፈላለግ በስደትም ሆኖ እምዬ ኢትዮጵያን ከውርደትና ከሁዋላቀርነት ለማውጣት የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ነው።ስለዚህ ሁላችንም ከእነዚህ አገር ወዳድ ሃይሎች ጎን በጋራ መቆም ይገባናል።

# አዲሱ ሃይማኖት

**Dawit Yilkal Fikir/HOF**

ከአክሱም ንጉስ ጀምሮ እስከ ሃይለስላሴ መንግስት ያልነበረ ይህ ሃይማኖት ብሔርተኝነት ይባላል።አፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ንጉስ በነበሩ ጊዜ በተለያየ ቦታ ንጉሳውያን ቢኖሩም እንኳን የኢትዮጵያ አንድነት መከበር እንዳለበት ያምኑ ነበር።ምንሊክን ጨምሮ።ነገር ግን በአሁኑ ስርዓት ኢትዮጵያን በተለያዩ ስሞች ተሰይሞ በአገሪቱ ከፍተኛ መከፋፈል እየታየ ነው።ይህ ነገር በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ አሁን የምናያትን ኢትዮጵያ ላናገኛት እንሰነባበታታለን።

የኢህአዴግ መንግስተ ፖሊሲዎች የአገሪቱን አንድነት የሚፈታተን ሲሆን፤ራሱን ከተጠያቂነት ነፃ ለማውጣት በሚያደርገው ጥረት የኢትዮጵያን ህዝብ በከፍተኛ ሁኔታ የሚጎዳ ነው።ብሔርተኝነትን ሰዎችን አንዱን ከአንዱ እየለየና እየከፋፈለ የእርስ በርስ ጦርነት እንዲነሳ የማድረግ ከፍተኛ ሃይል ያለው ዘረኝነት ነው።

ስለዚህ የኢትዮጵያን አንድነት ጠብቆ የሚያቆም ትክክለኛ መንግስት ያስፈልጋታል።በዘር የማይከፋፈል ሃብት ንብረቷን የማይዘርፍ ህዝቧን አሳልፎ የማይሰጥ ተጠያቂነትን የማይሸሽ ትክክለኛ መንግስት ያስፈልጋል።

# ወያኔ ግራ ተጋብቷል

**Fuad Yusuf Jemal/ Bayreuth**

ለጋራ ቤታችን ለሆነቺው አገራችን ኢትዮጵያና በአስተዳደር በደል ለከፋ ድህነት ለተዳረገው መላው ሕዝቦቿ የሚሆን አንዳችም ራዕይ ሳይኖረው ለመንግሥትነት ሥልጣን የበቃው የወያኔ ቡድን ላለፉት 23 ዓመታት ከግል ኑሮአቸው አሻግረው የአገርንና የወገንን ጥቅም ማየት የማይችሉ ወይም የማይፈልጉትን በዙሪያው አሰባስቦ እያካሄደ ካለው ዘርፈ ብዙ የሃብት ምዝበራ ወንጀል በተጨማሪ እየፈጸመ ያለው የመብት ጥሰትና አፈና ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም።

ሰሞኑን እያፈተለኩ በመውጣት ላይ ከሚገኙ ምስጥራዊ የድምጽ መረጃዎች ለማረጋገጥ እንደተቻለው ደግሞ ለጥቂቶች የሃብትና የብልጽግና ምንጭ የሆነው ሥልጣን ከእጃቸው እንዳይወጣ በአንድ በኩል በምርጫ ስም እንዴት አድርገው ሕዝቡን ቀፍድደው የምርጫው ተሳታፊ ማድረግ እንደሚችሉ ሲዶልቱና በሌላ በኩል ደግሞ በቁጥጥራቸው ሥር የሌሉትንና ለሥልጣናቸው ያሰጉናል ያሉዋቸውን የደሃዉን ልጅ በማጋፈጥ እንዴት በጦርነት እንደሚጨፈልቁዋቸው ሲመክሩ ተሰምተዋል።

ከወያኔው ቁንጮ አንዱ የሆነው በረከት ስምን በየደረጃው ላሉት የአገዛዙ ሹሞችና ካድሬዎች ባደረገው ገለፃ መሬትን የመንግሥት ባደረገው ኮሚኒስታዊ አዋጅ ምክንያት የመንግሥት ጭሰኛ ለመሆን የተፈረደበትን ሰፊውን አርሶ አደር “ተኛ ስንለው ይተኛል፤ ቁም ስንለው ይቆማል ፤ እንደፈለግን ብንበድለው እንኳ አያማርረንም ” እያለ ሲዘባበትበት ተደምጦአል ። በአንድ ለአምስት ኮሚንስታዊ አደረጃጀት ተጠርንፎ የወያኔ የንግድ ድርጅቶች ብቻ የሚያቀርቡትን ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ያለውዴታው እንዲራገፍበትና ከአቅሙ በላይ ዕዳ እንዲቀፈቅፍ የተፈረደበት የኢትዮጵያ አርሶ አደር በዚህ አይነት ንቀት ደረጃ የሚዘባበትበትን መሪ ከወያኔው በረከት ስምን በፊት ገጥሞት አያውቅም ። ለወደፊትም ሊያይ አይፈልግም ። ወያኔን ሥልጣን ላይ ለማምጣት የሰሜኑ ክፍለአገራችን አርሶ አደር የተጫወተው ሚና ተዘንግቶ በበረከት ስምን እንዲህ መዋረዱ እጅግ ያሳዝናል። ለነገሩ ከፍተኛ የህይወት መስዋዕትነት ከፍሎ ለድል ያበቃው የትግራይ ሕዝብ ቁም ስቅሉን እያየ አይደል ?

ሌላው አስገራሚ ክስተት በአገር ደህንነት ሥራ ላይ የተሰማሩ ዜጎች ባደረጉት ዝግ ስብሰባ ታማኝነታችን ለአገራችን ነው ወይስ የሥርዓቱን አገዛዝ ዕድሜ ለማራዘም? ብለው ላነሱት ጥያቄ የጠቅላይ ሚንስትር ተብዬው የህግ አማካሪ ጌታቸው ረዳ የሰጠው መልስ ነው። ደህንነት ብቻ ሳይሆን የመከላከያ ሠራዊትና ፖሊስ ጭማር ታማኝነታቸውና ግዴታቸው ሥርዓቱን ሥልጣን ላይ ማቆየት መሆን አለበት ሲል ጌታቸው እንቅጩን ነግሮአቸዋል ። በምላሹ “ላለፉት 23 አመታት እያደረግነው ያለው ይሄው ሆኖ ሳለ አሁን ምን ብታስቡ ነው ጥያቄ ያነሳችሁ?” የሚል ይመስላል ። ይባስ ብሎም ሥርአቱን ለመጠበቅ ያልቻለና በግንቦት 7 መንገድ የሚጓዝ ደህንነት ሠራተኛ የተስፋየ ገብረስላሴን ያህል የደህንነት እውቀት ቢኖረውም ሆነ እስራኤል አገር የዓመታት ስልጠና ያገኘ ቢሆን ዋጋ የለውም ብሏቸዋል።ወያኔ ግራ ገብቶታል።ስለዚህ አብዮት ልጆቿን

መብላት መጀመሩ ግልፅ እየሆነ በመምጣቱ ትግላችንን አጠናክረን ልንጓዝ ይገባል።

## ዜግነታዊ መብቶች

**Temesegen Sumoro Gebermariam/ Bischofsheim**

ሕዝብ ገዥዎች በቸርነታቸው ከሚወረውሩለት የመብትና የደህንነት ፍርፋሪ ውጭ በዜግነቱ ሊጠይቃቸው የሚገቡ መብቶች አሉት የሚል እምነት ዛሬም በሥልጣን ላይ ባሉት የሀገሪቱ ገዥዎች ዘንድ አይታወቅም፡፡ በመሆኑም ሕዝብ የገዛ ሃገሩና የገዛ ሕይወቱን በሚመለከቱ ጉዳዩች ላይ ለመምከር ለመወሰን መብት የለህም ተብሎ በባይተዋርነት እንዲኖር ተገዷል፡፡ ይህ ደግሞ ጉልበቱን እውቀቱንና ሃብቱን በነጻነት መንፈስ በማንቀሳቀስ በዓመት እየተባባሱ የሚሄዱትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቹን ማቃለል እንዳይቻል ትልቅ እንቅፋት ሆኖበታል፡፡

ዛሬ በሀገራችን ያለው ከችግሮቻችን ሁሉ መሠረታዊ የሆነው ችግር ከፖለቲካ ጉዳይ ጋር የተሳሰረው ችግር ሆኗል፡፡ ዛሬ በሀገራችን በአንድ በኩል ራሱን ከተገዥነት አላቆ ሙሉ የዜግነት መብቱ እንዲከበርለት የሚፈልግ ሕዝብና በሌላ በኩል የገዥነት አባዜውን አራግፎ ሕዝብ በዜግነቱ የሚጠይቃቸውን መብቶች ለማክበር ፈቃደኛ ያልሆነ መንግሥታዊ የአገዛዝ ሥርአት ተፋጠው ቆመዋል፡፡

ሕዝብ ባለቤትነቱን በተቀማበት ሃገር የተፈጥሮ መራቆትን የሚያስቆመው ጠፍቷል፡፡ የሀገርና የወገን ብሄራዊ ክብርና ጥቅም ጥቂት የስልጣን ሱሰኞችን ጥም ለማርካት ሲባል እየተረገጠና እየተቸረቸረ ነው፡፡ በጥቅሉ የሃገራችን ሕዝብ እንደ ዜጋ ታይቶ መብቶቹ እንዲከበሩለትና የገዛ ሕይወቱን በሚመለከቱ በማናቸውም ጉዳዩች ላይ የመወሰን ስልጣን እንዳይኖረው ለማድረግ ትግላችንን እንቀጥላለን፡፡ኢትዮጵያን እግዚአብሄር ይጠብቃት።

## የፕሬስ መብት- እንዴት?

**Yohannes Selamu Benti/HOF**

በኢትዮጵያ የፕሬስ መብት ግብዓተ-መሬት ከገባ 10 ዓመታት እየተጠጋ ነው።ከ1997 ዓ.ም ምርጫ ጋር ተያይዞ ነፍስ መዝራት ጀምረው የነበሩት የፕሬስ ውጤቶችም ያው ምርጫውን ተከትለው ግብዓተ መሬት ገብተዋል።የወያኔ መንግሰት ፕሬሱን ለምን እንደማይወደው ማስረዳት የዋህነት ይሆናል።

ወያኔ ለሙያቸው ክብር ያላቸው ጋዜጠኞችን በክሶች ብዛት፤ በእስርና እንግልት እንዲሁም ከአቅማቸው በላይ በሆነ የገንዘብ ቅጣት እንዲሸማቀቁ በማድረግ እውነት ዘጋቢ ስታጣ የኢትዮጵያ የመረጃ አየር በውሸት የተሞላ እንዲሆን አድርጎታል። ወያኔ በፈለገው መልክ ሊተረጉመው በሚችለው አንቀጽ ጋዜጠኞችን እያስፈራራና እያዋከበ ሀሳብን በነጻ የመግለጽ ነፃነት መብትን ይኸው እስካሁን ድረስ እንዳፈነ ይገኛል።

ወያኔ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ በኢትዮጵያ ለታሰሩ፥ ለተገደሉ፥ ለስደት ለተዳረጉ በርካታ ጋዜጠኞች ዋና ተጠያቂ ነው። የእስራት ፍርድ ተፈርዶባቸው በመማቀቅ ላይ የሚገኙ አሁንም በርካታ ናቸው። የተወሰኑትም ደግሞ ደብዛቸው እንዲጠፋ ተደርገዋል። በአገር ውስጥ የሚገኙ የመረጃ መረቦችን በማናለብኝነት ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር፤ ከውጭ አገራት የሚተላለፉ የሬድዮና የቴሌቪዥን ሞገዶችን በይፋ በማፈን ኢትዮጵያ አገራችን በመረጃ ከዓለም የተነጠለች ደሴት ለማድረግ ተግቶ እየሰራ ይገኛል። ነፃ-ፕሬስ ለነፃነት፤ ለፍትህና ለእኩልነት የሚኖረውን አስተዋፅኦ የሚገነዘቡ ገዢዎች ፕሬሱ ለአንባገነንነት አገዛዛቸው የሚመች ስለማይሆን ይፈሩታል፤ ይጠሉታል፤ ያጠፉታል። ወያኔም እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው።

ስለዚህ በኢትዮጵያ እውነተኛ ዴሞክራሲ ሰፍኖ የመናገርና ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ተረጋግጦ እስከናየው ትግላችንን መቀጠል ይኖርብናል።

## የሰቆቃ ኑሮ ይብቃ

**Kidest Asfaw Cherinet/ Schwalbach**

በአገራችን ኢትዮጵያ ዕለት ዕለት ችግሮች እየበዙ ነው።የወያኔ መንግስት ህዝቡን እያንገላታ እያሰረ በዛ ላይ የኑሮ ውድነቱ የጤና ችግር የስራ ማጣት ችግር ኢትዮጵያ ውስጥ የተለመደ ነገር ሆኗል።

የህዝቡ መብትና እኩልነት መከበሩ ቀርቶ ዜጋው በሃገር በዘርና በጎሳ ተገነጣጥሎ አገሪቱ ለእርስ በርስ እልቂት ተጋልጣ ትገኛለች።ወጣቱ በነፃነት እንዳይንቀሳቀስ የተማረውን ሃይል በማፈን በማሰር የራሱን ብቃት የሌላቸውን ሰዎች ስልጣን ላይ በመሾም የኢትዮጵያን እድገት ወደሁዋላ እየጎተተ ነው።በአጠቃላይ የወያኔ መንግስት መብትና ዴሞክራሲን ለፕሮፓጋንዳ መሳሪያነት እንጂ በተግባር ለኢትዮጵያ ህዝብ አላጎናፀፈም።

ስለዚህ መላው ህዝባችን እስከ መቼ ነው የስቃይ ኑሮ የምትኖረው?የሰቆቃ ኑሮ እንዲያከትም በአንድነት ተባብረን እንታገል-ጥሪዬ ነው።ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

## ወያኔ- ፀረ መድብለ ፓርቲ

**Roza Teshome/ Würzburg**

ወያኔ ባረቀቀው ህገ መንግስት እንኳን ራሱ መተዳደር አልቻለም።በህገ መንግስቱ አንቀፅ 45 መሰረት የመንግስተ አወቃቀር በሚለው ርዕስ “የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስርዓተ መንግስት ፓርላሜንታዊ ነው“ ይላል። ፓርላማ ካለ በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ በነጻ ምርጫ ፓርላማ የሚገቡ ፓርቲዎች አሉ ማለት ነው።

በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ግን እንደው ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ያህል በህገ መንግስቱ ሰፈረ እንጂ በተግባር ምንም እየሆነ አይደለም።በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፉትን ፓርቲዎች በጅምላ ሲያሻው የሻዕቢያ ተላላኪ ሲሻው ደግሞ ሽብርተኞችና የሽብር ድርጅቶች መጠቀሚያ ሌላም ሌላም ይላቸዋል።በአገር ውስጥ ሆነው እድሜውን ለሚያራዝሙለትም ድርጅቶች እንኳን ክብር የሌለው ነው።

ምርጫ በመጣ ቁጥር ሲያሸማቅቃቸው ሲወርድባቸው ቅንጣት ታህል አደብ የሌለው ስርዓት የፓርላሜንታዊ ስርዓት መሰረት የሆነውን የመድብለ ፓርቲ ስርዓት በአምባገነናዊ አገዛዝ ቀይሮ ከህገ መንግስቱ ጋር የማይጣጣም ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ ጨዋታ በመጫወት ላይ ነው።

ስለዚህ ለትክክለኛ የፓርላሜንታዊና የመድብለ ፓርቲ ስርዓት መመስረት ህዝባዊ ትግላችንን አጠናክረን መቀጠል

## ሰላም

**Asnakch Telahun/Würzburg**

**ሰላምሽ በዝቶልሽ ህዝብሽ ተደስቶ**
**ማየትን እሻለሁ አንድ ቀን ተሳክቶ**
**የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ሞልቶ**
**ሲሰራ በጋራ ለአገር አንድነት ተግቶ።**

**ችግርሽ ተወግዶ ህዝብሽ ጠግቦ ሲያድር**
**ሁሉም ተትረፍርፎ ሞልቶ ሲታይ በክብር**
**እልል ብለን በደስታ እንድንዘምር**
**ግድያው ይቁም ደም ማፋሰሱ ይቅር**
**ህዝብሽ በፍቅር እንጂ በሃይል ሳይበገር**
**በከንቱ በድካም ከህዝብ ከመቃቃር**
**በግዜው መላ ምት በአስቸኳይ እንፍጠር**
**ተለጋሽ ብቻ ሆነን በዓለም እንዳንቀር።**

# እስከመቼ የአምባገነኖችን ዉሸት ተሸክመን እንዘልቃለን???

**Tewodros Admasu/Schlüchtern**

በህዝብ ላይ መንግስታዊ አሻጥር እየተፈፀመ ነው::

ለጋሽ አገሮች ከእኛ የሚያገኙት ብሄራዊ ጥቅም ሞቅ ባለ ቁጥር ኢኮኖሚያችሁ በመቶ ይህን ያህል አድጓል ይሉናል::

ፖለቲካው የፖለቲካ ፓርቲዎች ማን እንደጠራቸው አይታወቅ ያንጫጩታል....ወያኔም ማን እንደወከላት አይታወቅ ፖለቲካዊ ማጭበርበር እና ኢኮኖሚያዊ ደላልነትን አፋፍማዋለች:: ለጋሽ አገሮች ከእኛ የሚያገኙት ብሄራዊ ጥቅም ሞቅ ባለ ቁጥር ኢኮኖሚያችሁ በመቶ ይህን ያህል አድጓል ይሉናል:: ወይ ፍርጃችን አቤቱታችን ከፖለቲካ ነጻነት እና ዲሞክራሲያዊነት ጎን ለጎን የመሰረታዊ አገልግሎቶች ጥያቄ ነው ... ይህ ደሞ ለየት ባለ መልኩ አብዮታዊ ነው:: ለጋሽ አገራት የሚያወጧቸው ሃሰተኛ ጻረ አፍሪካ ሪፖርቶች በተለይ የምስራቅ አፍሪካን ተገን አድርጎ የተመቻቸው የብሄራዊ ጥቅማቸው ፎርሙላ ስኬት የአምባገነኖችን እድሜ በማስረዘም ህዝብ እንዲጭበረበር የህዝብ ጥያቄዎች እንዲደናቀፉ ለገዢዎቻችን የልብ ልብ ሰቷቸዋል:: ለብሄራዊ ጥቅም አስጊ ይሆናሉ የተባሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን እስከማጨማደድ እየዘለቀ በኢጅ አዙር ህዝባዊ ጥያቄዎች እንዲታፈኑ እየተደረገ አምባገነናዊ አገዛዝን አፍልተውብናል እንሱ ለጋሽ አገራት::

መሰረታዊ ፍላጎቶች እና የአገልግሎት ፍጆታችን በበቂ ሁኔታ ባልተሟላበት አገር መንግስት ፕሮጀክት ለመጨረስ የገንዘብ እጥረት ገጠመኝ በሚልበት አገር ብሄራዊ ባንክ የውጪ ምንዛሬ የለኝም በሚልበት እና የመንግስት ካዝና ባዶ ሆኖ በዕቃ ግምጃ ቤት ሰነድ ጨረታ ከቱጃሮች መንግስት በሚበደርባት አገር ጥቂት ፖለቲካው የወለዳቸው ሃብታሞች እጅግ ብዙ የኢኮኖሚ ድቀት ያፈራቸው ደሃዎች በፈሉበት አገር ምን አይነት የኢኮኖሚ እድገት እንደተመዘገበ አነጋጋሪ ነው:; እስከመቼ የአምባገነኖችን ደጋፊዎች ዉሸት ተሸክመን እንዘልቃለን ???

# ፍትህ ለሀይማኖታችን እና ለኮሚቴዎቻችን

**Adem noormohamed/ Schlüchtern**

ከሁለት አመት በፊት ነበር ህዝበ ሙስሊሙ መንግስት በሀይማኖታችን ጣልቃ አይግባ ሲል ጥያቄ ያቀረበው። ከመነሻው ህገመንግስታዊና በቀላሉ መፈታት የሚችሉ ግን ደግሞ መሰረታዊ ጥያቄወችን ነበር የሙስሊሙ ህብረተሰብ ጥያቄ አድርጎ የተነሳው።እነዚህ በዋናነት ሶስት ግልፅ ምላሽ የሚፈልጉ ጥያቄወች ሰሚ ጆሮ አተው ጥያቄውም ሳይመለስ ለጥያቄው መልስ የሚያስገኙ የመፍሄ አፈላላጊ ኮሚቴወቸም በመንግስት ነኝ በሚለው የማፍያ ቡድን በማናለብኝነት በማሰርና ነገሩን ወደሌላ አቅጣጫ በመምራት ዛሬ ላይ እንዲደርስ አድርጎታል።

ከወረቀት ውጭ ምንም ህግ እና ህገመንግስታዊ መብት የማይጠበቅባት የፍርድ እና የፍርድ ቤት ነፃነት የሌለባት ሀገር መሆኗን የወያኔ መንግስት በግልፅ አሳይቶናል። ጥያቄው እየታወቀ ህዝበ ሙስሊሙ ምን እንደሚፈልግ ግልፅ ሆኖ እያለ ግን ወያኔ ለርካሽ ፖለቲካው መጠቀሚያ ለማድረግ በከፍተኛ ሁኔታ ሰርቷል። ንፁህን የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴወቻችን ምንም እንዳላደረጉ የሚታወቅ ቢሆንም፣ ጥያቄው ግልፅና ህገመንግስታዊ መሆኑ ቢታወቅም ወያኔ ግን ጥያቄውን ሌላመልክ ለማሰጠት በተደጋጋሚ ፊልም እየሰራ ይባስ ብሎ ንፁህን የሙስሊም ልጆችን በማናለብኝነት በራሱ ቴሌብዥን እጃቸውን ይፊጥኝ እያሰረ በማቅረብ አምባገነንነቱን አሳይቷል።

ኮሚቴዎቻችን በህዝበ ሙስሊሙ በግልፅ የተወከሉ እና ህገመንግስቱን መሰረት በማድረግ ህዝብንና ሀይማኖቱን ወክለው መንግሰት ተብሎ ካለው ጋር ለመደራደር የሞከሩ ቢሆኑም ነገሩ ያስፈራው አምባ ገነኑ ወያኔ በፍጹም ውሸት ለድርድር ቁጭ ብሎ ሲደራደር የነበራቸውን የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴዎች ሁኔታው እሱ በፈለገው መንገድ አልሄድ ስላለው ብቻ አሸባሪ ሲል አንዴ ከግብጽ ሙስሊም ድራዘርስ ጋር ሌላ ጊዜ ከ አልሸባብ ጋር የፈለገውን አሸባሪ ስም እየጠራ ገና ፍርድ ቤት ያለጣራውን እና ምንም እውነት የሌለውን ባደባባይ በራሱ ቲቢ አሸባሪ በማለት ፍጹም ሰላማዊና ንጹሀን ወንድሞችን እያሰቃየ ይገኛል።

ባለፉት ሁለት አመታት ኮሚቴዎቻችን ያላዩት ስቃይ፤ ያልሆኑት ነገር የለም። በእስር ቤት እኛ አሸባሪ ነን፣ ጥያቄያችን ሌላ አላማ አለው ብላችሁ እመኑ በማለት ወያኔ የቁም ስቃይ እያደረሰባቸው ይገኛል። ኮሚቴዎቻችንም ሳይፈቱ ጥያቄዎቻችንም ሳይመለሱ ህዝበ ሙስሊሙ በፍጹም ወደኋላ እንደማይል እና አሁንም ከንጹሀን ወንድሞቹ ጋር እንደሆነ እያሳየ ነው። ወያኔ ወዶም ሆነ ተገዶ ጥያቄዎቻችንን እና መሪዎቻችንን እስኪፈታ ድረስ ጩኸታችን፣ ሰላማዊ ተቃውሞኣችን ዛሬም ነገም አይቆምም።

# እምየ ኢትዮጵያ

**Ibrahim Yusuf Suleyman/ Alsfeld**

**አገሬ ኢትዮጵያ ስርዓት የላት ህግ**
**ወያኔ አዝማሪው ያረዳት እንደ በግ።**
**መኖሯን አታውቅም ተረግጣ ተንቃ**
**በንፁሃን ዜጎች በደም ተጨማልቃ**
**መውጫ በር የጠፋት ተዘግታ በሲቃ**
**ውሎዋ የሆነ ለቅሶና ሰቆቃ**
**አለሁ ትበል እንጂ መያዟን የት-**
**አውቃ።**

**ፋሽስቱ ኢጣሊያ ሌላውም የሚያውቅሽ**
**የተከበርኩ ስትይ ልትሆኚ የተዋረድሽ**
**አረዱሽ ቆረሱሽ ይኸው ሸነሸኑሽ**
**መሬትሽ እንደ ሰው ለሱዳን ሄደብሽ።**

**ንገሪኝ አገሬ ቁርጡን ልወቀው**
**ግፉና ሰቆቃው መቼ ነው ሚያበቃው**
**ምንድነው መላው ንገሪኝ አገሬ**
**ምላሹንም ስጪኝ አሁኑኑ ዛሬ**
**ዝምታሽ አይብዛ ንገሪኝ አገሬ።**
**ልጆችሽ ነን እንጂ አይደለን ደመኛ**
**እንታደግሻለን አርጅተን ሳንተኛ።**

# ከመለስ ጋር የሞተው ሕወሃት

**Sara Mesfin/Viernheim**

ይህ የያዝነው ወርሓ የካቲት "የህወሓት ልደት የትግራይ ህዝብ ልደት ነው፣ ህወሓት ብቸኛ የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ነው፣ የትግራይ ህዝብ ታሪክ ከደደቢት ይጀምራል፣ የህወሓት አላማና ፍላጎት የትግራይ ህዝብ አላማና ፍላጎት ነው፣ የትግራይ ህዝብ ከህወሓት ሌላ አማራጭ የለውም ዙሪያው ሁሉ ገደል ወይም ጠላት ነው፣ በአጠቃላይ የትግራይ ህዝብ ህልውና ከህወሓት ህልውና ጋር የተቆራኘና ድርጅቱ ስልጣን ላይ ሲኖር ትግራይም የምትኖር ድርጅቱ ከጠፋ ወይም ስልጣን ላይ ከሌለ ደግሞ የትግራይ ህዝብም አብሮ የሚጠፋ ነው"........እያሉ በመስበክ በሰማእታት መቃብር ላይ ቆሞው የውሸት ድራማ የሚሰሩበት፣ በትግራይ ህዝብ ደምና አንጡራ ሃብት ላይ የሚነግዱበት፣ በድምሩ "ጅሮውን ቆርጠው የሰጡት ውሻ ሥጋ የሰጡት ይመስለዋል" እንዲሉ የትግራይ ህዝብ ብሄራዊ ክብሩ፣ ዳር ድንበሩንና ብሄራዊ ጥቅሙን ለባዕድ ሸጠው ሲያበቁ ነፃ አውጥተናሃል!! ልማት አምጥተንልሃል!! እያሉ የሚዘምሩበትና የሚመፃደቁበት የካቲት ፲፩ በዓል እየመጣ ነው። ይህ ዓይነቱ ጭፍን የፕሮፓጋንዳ መርዝ ደግሞ ዛሬ የመጣ ባህል አይደለም። ህወሓት ከተፈጠረበት ቀን አንስቶ እስካሁን ድረስ ለአርባ ዓመታት ያህል ለጀሮ እስከሚሰለች ድረስ በካድሬዎቹ አማካይነት ነጋ ጠባ በዜዎች በተቀደሰች ምድር ትግራይ በአሁኑ በሃያ አንደኛ ክፍለ ዘመን የሚሰበክ የደደቢት የአደንቁረህ ግዛ ፍልስፍና መሆኑን ተራ የገጠር እረኛም ሳይቀር ያውቀዋል።

ይሁን እንጂ ህወሓት ከድርጅትነት ወደ ቡድናዊ አምባ ገነንነት፣ በኋላም ከቡድናዊ አገዛዝ ወደ ፍፁም የቤተሰባዊ መዝርፊያና የማፊኛ የግል ኩባንያ ሆኖ ከተሸጋገረ ወዲህ እነሆ ዓሰርት ዓመታት አስቆጥሯል። በመጨረሻም "ጊዜ ዳኛ ታሪክ ምስክሩ ነውና" ድርጅቱ ከባለቤቱ ከቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ጋር አብሮ ግብኣተ መሬት ገብቷል። ላይመለስ አብሮ ተቀብሯል። አሁን ያለው "በድርቆሽ የተሞላ ህይወት የሌለው የቆዳ ግሳንግስ ወደ(ዓርሲ)" ተለውጦ ባንድ በኩል በአቶ ስብሓት ነጋ የ80 ዓመት ጎበዝ አለቃ የሚመራ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኤርትራውያን የሚገፋ አሮጌ ጋሪና በወታደር የሚጠበቅ የደረቀ ሬሳ ሆኖ ቀርቷል" የሚሉ ብዙዎች በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው።

# መሬታችንን በሚስጥር ለሱዳን የሚሰ ጡበት "ስምምነት" ምክ ንያቱ ምንድን ነው ?

**Behailu Girma/ Schöneck**

አቶ መለስ እና አቶ ኃይለማርያም በአጠቃላይ "በድንበር ስምምነቱ" ዙሪያ እያቀረቡት የነበረው እና ያለው የውሸት ፍብረካ ድሪቶ ሪፖርት እውነታውን ለመደበቅ ከሚሽመደመደው ድሁር አስተሳሰባቸው ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም:: እውነተኛው የድንበር መስጠት ስምምነት እ.ኤ.አ በ2008 ተጠናቋል:: በምንም ዓይነት መልኩ ቢሆን አቶ መለስ "ግዙፍ የሆነ መሬት ከአማራ ክልል" ቆርሰው ፈርመው፣ አትመው እና አሽገው ለሱዳን መስጠታቸውና በድብቅ "በድብቅ ተይዞ እንዲቆይ" መጣራቸው የሚያጠያየቅ ጉዳይ አይደለም:: እ.ኤ.አ በ2014 የኢትዮጵያ የይስሙላው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የአቶ መለስን የበከተ ውሸት እንደተለመደው "በሀሰት መጋረጃ ደብቀው" ለዘላለም ለማቆየት በማሰብ ሌላ ዘርዘር ያለ ፖለቲካዊ ድራማ ለመተወን በመውተርተር ላይ ይገኛሉ:: አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ እና ጌቶቻቸው የኢትዮጵያን ህዝብ ሊያታልሉ፣ ሊያጭበረብሩ እና በውሸት ሊደልሉ የሚችሉ ይመስላቸዋል:: እነዚህ የዕኩይ ምግባር ባለቤቶች መሬትን ያህል ነገር በድብቅ ሸፍኖ የመስጠት ጨዋታቸውን ኢትዮጵያውያን የማያውቁ እና የማይገነዘቡ ሞኞች አድርገው ይቆጥራሉ:: እነርሱ ይህን የሞኝነት ጨዋታቸውን እንደፈለጉ መጫወት ይችላሉ፣ ሆኖም ግን አቶ ኃይለማርያም አንድ ጥያቄ እንዲመልሱልኝ እፈልጋለሁ፣ ይኸውም " 'ከአማራ ክልል ግዙፍ መሬቶችን ቆርሰው የሰጡት' "ድብቅ የሚስጥር ስምምነቶችን የት እንዳስቀመጧቸው ሊያሳዩኝ ይችላሉን? አቶ መለስ እ.ኤ.አ በ2008 እና አሁን ደግሞ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ እና የዕኩይ ምግባር አጋሮችዎ የድብቅ ስምምነቶችን ከህዝብ ፊት ደብቃችሁ ከፊታችሁ ላይ የውሸት መጋረጃ በማድረግ ለመዝለቅ የምትፈልጉት ለምንድን ነው?" ከአገር መሬት ቆርሳችሁ ለባዕድ አገር ስትሰጡ በአገሪቱ ህገመንግስት ስልጣን ለተሰጠው ፓርላማ (ለተወካዮች ምክር ቤት) ተብዬው ለይስሙላ እንኳን ቢሆን መቅረብ የለበትምን"? ህገመንግስቱ የሚለው ሌላ የስርዓቱ ቁንጮዎች የሚያደርጉት ሌላ! አራምባ እና ቆቦ! ድብቅነት በኢትዮጵያ በመግዛት ላይ ላለው ገዥው አካል ዋና መለያ ባህሪው ነው:: ነገሮችን ደብቆ በመያዝ እያንዳንዱን በማሞኘት ላይ ይገኛሉ:: አቶ መለስ በህይወት በነበሩበት ጊዜ እና በአሁኑ ጊዜ ያሉት ሎሌዎቻቸው ደግሞ የቅብብሎሽ

ዱላውን ከጌታቸው ራዕይ በመቀበል በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያሳዩ ያሉት ንቀት የህዝቡን ምንነት ሳይገመግሙ እና ሳይረዱ በራቁት ገላው ላይ ሱፍ እየጎተቱ መሆኑን በውል ሊያጤኑት ይገባል፡፡

አቶ መለስ እና ጋሻጃግሬዎቻቸው አሰብን እና ባድመን በቤሣ ቁርጥራጮች ካስረከቡ በኋላ ዝምታ ብቻ መልስ ስላገኙ ከዚያ ነገር አንድ ቁም ነገር ተምረዋል፡፡ ይኸውም ኢትዮጵያውያንን እና የኢትዮጵያን ግዛት የእነርሱ የግል እንደፈለጉ የሚለውጧት፣ የሚሸጧት የህግ ተጠያቂነት የሌለበት የግል ንብረታቸው መሆኗን አረጋገጡ፡፡

## ለነጻነታችን አንድ ሆነን መታገል ይኖርብናል !!!

**Girum Kelemu & Netsanet Mamo/Groß-Gerau**

የተለያየ የፖለቲካ አቋም ሊኖረን ይችላል፣ የተለያዩ ብሄሮች ልጆችም ልንሆን እንችላለን፣ ኢትዮጵያውያን በመሆናችን ግን እነዚህ ሁሉ ነገሮች በህልውናችን ላይ አንዳች ጥላ ማጥላት የለባቸውም። ደግሞም ከተቀራረብን እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሊታረቁና ሁላችንንም የሚያስማሙ ሀሳቦችን ለመፍጠር ይችላል።

የአፍሪካ የነፃነት ምሳሌ የሆንን ዜጎች ህብረ ብሄራዊ ውበታችንን በእያንዳንዳችን ማንነታችን ላይ ካለው ኢትዮጵያዊነታችን ጋር የተጣበቁ የጋራ ተቀፅላዎችችን በማጥፋት የትም ቦታ አንገታችንን ቀና አድረገን ለመኖር ምቹ ሁኔታዎችን ልንፈጥርበት ይገባል። ልዩነቶቻችን በማቻቻል የትም ይሁን የት በአንድነት መስራቱ ለዜጎቿ ለኑሮ ምቹ የሆንች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ዳግም ኢትዮጵያን ታላቅ ለማድረግ ያስችለናል።

ይኸው ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያስተዳድረው ወያኔ/ህውሃት የህዝብ መብት በመንቀፍ፣ ዘረኝነትን በማስፋፋት፣ ሀገርን በመከፋፈል፣ ጎሰኝነትን በማስተማር፣ ሀገር በመዝረፍ፣ ሀገርን በመሸጥ፣ ሰውን ከሚኖርበት ቅዬ በማፈናቀል፣ በመቻቻል እንዳይኖር በማድረግ፣ ዘር ከዘር ጥላቻን ማስፈን ቀጥሎበት ሃያ ሁለት ዓምታትን አስቆጠረ። እስከመቼ ይኸን ነገር ዝም ብለን ማየት እንችላለን? ነፃነታችንን የቀሙን የወያኔ ዘረኞች ነፃነታችንን እንደቀሙን ለረዥም አመታት ለመግዛት እንዲመቻቸው በዘር፣ በቋንቋ፣ በክልልና በሃይማኖት ከፋፍለውን ከሃያ አንድ ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የጀመሩትን እስራት፣ ስደት፣ ግድያና ዝርፍያ አሁንም እንደቀጠሉ ነው። የወያኔ ዘረኞች ነፃነታችንን ቀምተው እየገዙን ቢሆንም ገዛናቸው ብለው እጃቸውን አጣጥፈው አልተቀመጡም። ዜጎች ነፃነታቸውንና መብታቸውን እንዳይጠይቁ አፋቸውን ያዘጋሉ፣ አንዱ ለሌላው እንዳይቆም ሀገር፣ ባንዲራና ኢትዮጵያዊነት የሚባሉ ትላልቆቹን የጋራ እሴቶቻችንን በየቀኑ ያፈረሳሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ የዘር በትር አለንጋ የሚደርስበት ግርፋት፣ ስቃይ፣ ረሃብ፣ ስደት፣ እንግልት በራሱ በህዝቡ ላይ ነው። ስለዚህ ህዝቡ ራሱ ለራሱ ነፃነት በእምቢ አልገዛም ባይነት የሚነሳበት ጊዜው አሁን ነው። ነፃነትን ከነፃ አውጭዎች በመጠበቅ እስከመቼ የወያኔ የጥይት ሰለባዎች እንሆናለን? ወገን ሁሉ ለራሱ ነፃነት፣ ህልውና ሲል የለውጡ እንቅስቃሴ ታጋይ የመሆን ኢትዮጵያዊ ግዴታውን እንዲፈጽም ጥሪ ማድረግ ይገባል።

ለሀገሩ፣ ለማንነቱ መሰዋትነት ለመሆን እንደሚኮራ ሁሉ ሀገሩም በሱ ትኮራለች። ወያኔ በ22 ዓመት ውስጥ የሰራው ወንጀል በወገናችን ላይ እንዲህ በቃላት ተዘርዝሮ አያልቅም። ይህ አልበቃ ብሎ ታዲያ ምንድ ነው አንድ ሆንን ከመታገል ፈንታ መለያየትን መረጥን!

## አንቺ አገሬ

**Beza Amanuel /Würzburg**

**ብወጣ ብወርድ በኤንትሬ**
**ብሞጫጭር በበሬ**
**ከልኩ አያልፍ የእኔ ነገር**
**የለም እድገት ብሎ ነገር**
**ዶሮ ብታልም ጥሬዋን**
**ሆኖ ቀረ ብቻ መመኘትን**

**መሬት ላራሹ ስል ስጮህ**
**ቀረሁ እንደ ህፃን ስድህ**
**ለማን ልንገር ብዬ ሳስብ ስመክር**
**ለዚያው የጫካ መምህር**
**ዴሞክራሲ እያለ የሚደሰኩር**

**እምባዬን አፈሰሰስኩ ለዴሞክራሲ**
**አባዜ**
**መልሴ ሆኖ ቀረ እንጂ ትካዜ**
**ለፍቼ አሳድጌ ያደረስኩትን**
**ተነጠቅኩ በወያኔ ልጄን**
**ታዲያ ለማነው አቤቱታው**

**ጉልበት አለኝ ይላል ጉልበት-**
**ጉልበት የአምላክ ነው**
**ፈጣሪ አምላካችን የሁሉ የበላይ**
**ነው**
**ያሻኝን ልናገር አንደበቴ ተከፍቶ**
**ፍራቻና ሽብር ከመካከላችን ጠፍቶ**

**እንዳሻን ወጥተን እንዳሻን**
**እንድንገባ**
**የተሰደደድነውም እንዳንሆን ሰለባ**

**ሰላምን የምንሻ አገርን የምንወድ**
**ድምፃችን ይሰማ ወያኔ እንዲወገድ።**

## በሚመሩት ህዝብ ላይ የተሳለቁ መሪ

**Belay Fikire/ Ehringshausen**

የአማራ ክልል ም/ ፕሬዚዳንት እና የብአዴን ጽ/ቤት ሃላፊ የሆኑት አቶ አለምነው መኮንን "የአማራው ህዝብ ሰንፋጭ የሆነ ትምክተኝነት የተጠናወተው በመሆኑ በቤንሻንጉልና በሌሎችም ቦታዎች ለመሰደዱ ምክንያት ሆኖታል" በማለት፣ ለብአዴን ካድሬዎች መናገራቸው ይታወቃል ። ካድሬዎቹ "የአማራው ህዝብ ለምን ይሰደዳል? ለምን በእየክልሉ ጥቃት ይደርስበታል? አማራውን ከጥቃት ለመከላከል ለምን ሙከራ አይደረግም በማለት ጥያቄ ሲያቀርቡ ፣መሪ ተብየው ግን የአማራው ህዝብ በቅድሚያ እንዳይሰደድ ለማድረግ ስራ እየተሰራ ነው፣ ነገር ግን ከተሰደደ በሁዋላም ቢሆንም ሰንፋጭ የሆነውን ትምክህተኝነቱን በመተው ከሌላው ጋር ለመኖር መልመድ አለበት አሉ። አክለውም አማራው "በባዶ እግሩ እየሄደ የሚናገረው ንግግር ግን መርዝ ነው" በማለት ተሳለቁ። ፣ ይሄ መርዝ ንግግሩ አንድ የሚያደርግ አይደለም ሲሉም ተደምጠዋል።

ከኢትዮጵያውያን ጋር አብሮ ለመኖር አማራው የትምክህት ለሃጩን ማራገፍ አለበት ያሉት አቶ አለምነው፣ ይሄ ለሃጭ ሳይራገፍ በጋራ መኖር አይቻልም ሲሉ ድምድመዋል። ማንኛውም ስም ያወጣ ሙትቻ ፓርቲ ሁሉ መንገሻው አማራ ክልል ነው ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ ምክንያቱንም ሲገልጹ ትምክህትን እንደ ምግብ ስለሚመገበው አሉ።። ያንን ምግብ እየተመገበ ያቅራራልም በማለት አፌዘዋል ።በሚመራው ህዝብ ላይ የሚሳለቅ እንዲህ አይነት ትምክህተኛ መሪ ምንም እንኳን ትክክለኛ ፍርድ ባይኖርም ባስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርብ መደረግ አለበት።

## ከሱዳን ጋር የተደረገው ህገወጥ ስምምነት ተፈጻሚነት ሊኖረው አይችልም

**Mikyas Befekadu/Schlüchtern**

በአቶ መለስ፣ አቶ ኃይለማርያም እና ጓዶቻቸው የተደረገው ህገወጥ ስምምነት ተፈጻሚነት የማይኖረው ቢሆንም በመጠኑም ቢሆን አሳስቦኛል፣ ሆኖም ግን በግልጽ እና ጥልቀት ባለው መንገድ ሳገናዝበው ብዙ የሚያሳስበኝ አይሆንም:: "ስምምነት" እየተባለ ስለሚጠራው ጉዳይ ብዙ የሚታወቁ ድብቆች አሉ::

ስምምነቶቹን ካባ ደርበው ትልቅ ነገርን እንደፈረሙ እናውቃለን:: ሆኖም ግን ምን እንደደበቁ በእርግጠኝነት ለመናገር አይቻልም:: ስምምነቶቹን ከህግ አግባብ ውጭ በሙስና እንዳደረጉ እናውቃለን፣ ሆኖም ግን የሙስናውን ስፋት እና ጥልቀት እስከምን ድረስ እንደሆነ በግልጽ አይታወቅም:: የስምምነት ሰነዶች ሲፈረሙ ሁሉንም ዓይነት ያካተቱ ማጭበርበሮች እንዳሉ እናውቃለን፣ ሆኖም ግን የማታለል፣ የማጭበርበር እና የመሰሪነት ዓይነቶችን አናውቅም:: በድብቅ የተፈረሙት ስምምነቶች እና አሁንም ሚስጥር ሆነው የተያዙት ድሁር እና ኮሳሳ ስምምነቶች ወደፊት በጊዜ ሂደት እርቃናቸውን ወጥተው ሚስጥሩ ግልጽ የሚሆንበት ጊዜ ይመጣል:: "እውነት ለዘላለም ተቀብራ እንደማትኖር ሁሉ ተንኮልም በዙፋን ላይ ለዘላለም ተቀምጣ አትኖርም"::

የኢትዮጵያ የግዛት ሉዓላዊነት አንድነት በምንም ዓይነት መልኩ ለድርድር አይቀርብም:: ኢትዮጵያ በክልል መከፋፈል የለባትም፣ "በጎሳ ፌዴራሊዝም" መበጣጠስ የለባትም፣ ወይም ደግሞ በድንበር መካለል ሰበብ "ስምምነት" መሰረት ግዛቷ መሸጥ የለበትም:: ወደ የግዛት ሉዓላዊነት አንድነቷ የተጠበቀች ኢትዮጵያ ስንመጣ ኦሮሞ ኢትዮጵያ የለችም፣ አማራ ኢትዮጵያ የለችም፣ ትግሬ ኢትዮጵያ የለችም፣ ጉራጌ ኢትዮጵያ የለችም... ወይም ደግሞ ጋምቤላ ኢትዮጵያ የለችም:: በቀላሉ አነጋገር የኢትዮጵያ ህዘቦች ኢትዮጵያ ናት ያለችው:: በሉዓላዊነት የግዛት አንድነት ዙሪያ በመሰባሰብ ኢትዮጵያ የማትከፈል እና የማትከፋፈል መሆኗን በማመን መተባበር አለብን::

ምንጊዜም ቢሆን ጠንቃቃ ሆነን መገኘት አለብን፣ እናም ከመቃብር አፋፍ ላይ ሆነው ለማትረፍ የሚፈልጉ ተንኮለኛ ጭራቆችን እራሳቸው በመቃብር ውስጥ እንዲቀሩ እናድርግ:: አምላክ ሁላችንንም አንድ አድርጎ እንደፈጠረን ሁሉ በፍቅር እና በመከባበር በአንድነት በመኖር ለአምባገነንነት፣ ለጨፍጫፊነት፣ ለመለያየት ቦታ መስጠት የለብንም::

ዛሬም አንዲት ኢትዮጵያ! ነገም አንዲት ኢትዮጵያ! ለዘላለምም አንዲት ኢትዮጵያ!!!

## የብሔር ፖለቲካ ጠባብነት ነው

**Daniel Theodros/Viernheim**

ኢትዮጵያ ምሳሌ ልትሆንበት የምትችልበት ነገር ሃይማኖት ብቻ አይደለም:: ኢትዮጵያ ከሰማንያ በላይ ብሔር ብሔረሰቦችን በውስጧ አቅፋ የያዘች አገር ናት:: አይደለም ሰማንያ ቀርቶ ሁለት

ብሔረሰቦች ያሉባቸው አገሮች ግጭት ውስጥ ሲገቡ እናያለን፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ጥቃቅን ግጭቶች የሉም ማለት ባንችልም፣ በአጠቃላይ ግን ለመኖር የሚያዳግት ግጭት ግን አስተናግዳ አታውቅም፡፡ ይህ ታሪካችን የሚያኮራን ቢሆንም፣ አሁን አሁን ግን የሚስተዋሉት ነገሮች ሃይ ሊባሉ የሚገባቸው ናቸው፡፡

ስለአብሮ መኖር ታሪካችን የማንጠነቀቅለት ከሆነ ይህ አኩሪ ታሪክ ሊበላሽና ሊጠፋ ይችላል፡፡ በተለያዩ ወቅቶች በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚነሱ የብሔር ግጭቶች የጉዳዩን አሳሳቢነት ሊያሳዩን ይችላሉ፡፡

በተለይም አገሪቱ ተስፋ የምታደርግባቸው እነዚህ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጠባብ በሆነ የብሔር ፖለቲካ ውስጥ ገብተው ሲጋጩና ሲበጣበጡ ማየት አሳፋሪ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የአማራ ብቻ አይደለችም፤ ኢትዮጵያ የኦሮሞ ብቻም አይደለችም፤ ኢትዮጵያ የደቡብ ብቻም አይደለችም፤ ኢትዮጵያ የትግራይ ብቻም አይደለችም፤ ኢትዮጵያ የሁሉም ናት፡፡

ስለዚህ አንዱ ብሔር ከአንዱ ብሔር አይበልጥም፡፡ አንዱ ብሔር ከአንዱ ብሔርም አያንስም፡፡ ሁሉም እኩል ነው፡፡ አንዱ ከአንዱ ይሻላል በሚል ጽንፈኛ የብሔር ፖለቲካ አንድነታችንን ማፍረስ አይገባንም፡፡ የሁሉም ብሔሮች መገኛ የሆነችውን ኢትዮጵያን መመልከት ይገባል፡፡ በዚህም ረገድ ራሳችንን መሳል ተገቢ ነው፡፡ ያለበለዚያ ግን በየጊዜው እየዶለዶምን ሄደን አንድነታችንን ልናጣው እንችላለን፡፡ ስለዚህ ሰዎች ሐሳባቸውን በማንፀባረቃቸው ምክንያት በጠላትነት ሊፈረጁ አይገባም፡፡ ምክንያቱም ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ሕገ መንግሥታዊ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሯዊም ነውና፡፡ ጽንፈኛ የሆነ አመለካከት በመያዝ የእኔ መንገድ ብቻ ነው ትክክል ማለት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ኋላቀር የሆነ ብቻ ሳይሆን የማያስኬድ ነው፡፡ ስለዚህ ራስን በአንድ ሳጥን ውስጥ ጨምሮ እኔ ብቻ ያልኩት ይሁን ማለት አንድነታችንን ሸርሽሮ በኋላ ባዶ ሊያስቀረን ይችላል፡፡ በመሆኑም በፖለቲካው እንዲሁም በሌላውም ጉዳይ የእኔ ሐሳብ ብቻ ይንገሥ ማለት ማንንም የትም አያደርስም፡፡ ስለዚህ በየትኛውም ጉዳይ ላይ ጽንፈኝነትን በማስወገድ አንድነታችንን ሊያጠናክሩ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ ብናተኩር ሁላችንንም ይጠቅመናል ፡፡

## የሙስናው ቁንጮ

Nebyu Teferi Mekonnen/ Flörsheim

ወያኔን ለማልመድ ባጥንት ባባብለው
እስከነ አጥንቱ እጄን ቀረጠፈው

የአባድር ጅቦች የሰው ስጋ እርማቸው
ይህ አረመኔ አውሬ በጣም አብግኗቸው
ጥለው ቀረጠፉት ምህላውን
አፍርሰው።

ጉድፈላ ጉድፈላ ጉድ ፈላ ዘንድሮ
መደመር ሳይማር መቀነስ ተምሮ
የሙስናው ቁንጮ በላን አሸብሮ።

ሞሳሹን ወይያኔ እዩት ሲያምታታ
አይጥ በበላ ዳዋውን ሲመታ።
ደግሞም ከወያኔ ወያኔ ይመርጣል
ቆርኪ እየጫነ መኮንኖች ይላል
እየተበላሉም አንዱ ባንዱ ይስቃል።

አገርን ለባዕድ ሸላሚ ቸርቻሪ
ህዝቧን ለባርነት ስደት አባራሪ
እየጨፈጨፈ በግፍ ዜጋ አሳሪ
በውስጥም በውጭም ዜጋን አሳፋሪ
በሽብርተኛ ስም ወገን አሸባሪ
ጎጠኛው ወራሪ ወያኔ መሰሪ
የእጁን ያገኛታል አገራችን ኩሪ
ኢትዮጵያ አገራችን ለዘላለም ኑሪ።

## ስማኝ ያገሬ ሰው

Sara Mihretu Belay/Würzburg

ድምፅን አንድ አድርጎ ካልተናገረ ሰው
መረረኝ ሰለቸኝ ብሎ ካልጮኸ ሰው
ስርዓቱ ይቀየር በቃኝ ካላለ ሰው
ሰላማዊ ባሪያ መሆን ካስደሰተው
እንደምን ሆኖ ነው ነፃነት ሚገኘው

ራሱ የሚከስ ራሱ የሚያስር
ራሱ የሚዳኝ ከሃገር ሚያባርር
የወያኔ ቁንጮ የወያኔ ግብረአበር

በለኮሰው እሳት መለብለቡ አይቀርም
የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ እንዲህ ፈሶ
አይቀርም
የሚሰማ ሲጠፋ የሚደርስ ወዳጅ
ድምፅን ማሰማቱ ካልሆነ የሚበጅ

መሆን የለበትም ተስፋ ቆራጭ
መጋተር ብቻ ነው ያለን አማራጭ

እይታህን አጥራ ተባበር ወገኔ
ተሟገት ተጋተር በኢትዮጵያዊ ወኔ
ለጣሊያን አልወደቅክም እንኩዋን
ለወያኔ።

## ማረሚያ

*ባለፈው በ2ኛ ዓመት ቁጥር 8 እትማችን ገጽ 7 ላይ ኢትዮጵያዊው የፈጠራ ባለቤት በጀርመን በሚል ርዕስ ለንባብ ባቀረብነው ፅሁፍ ውስጥ የፈጠራ ባለቤቱ የአቶ ነብዩ ተፈሪ መኮንን ዕድሜ 36 ሳይሆን 43 ዓመት መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን። ለተፈጠረው የስሌት ስህተት ጥላ መፅሔት አንባቢዎቿን ይቅርታ ትጠይቃለች።*

*ከዝግጅት ክፍሉ*




Picture source: google.com

# Democracy and Ethiopia

**Melese Sebsibe/ HOF**

Ethiopian leaders are saying now adays, they follow and make democracy in the country.so, is there really democracy in Ethiopia?

No there is no democracy in the country because democracy is the right to speak, live, work, elect and to be elected and etc. but in Ethiopia ,the government obliged us to follow its regimeor to be a member of the ruling party.to be a member of the ruling party is an obligation. If you don`t supports the ruling junta and don`t need to be a member of TPLF/ EPRDF, you will never ever get a work.

In Ethiopia there is one important thing, which is the constitution. There is a democratic constitution, but it is only in paper and uses only for propaganda. It is just a fake. They prepared the constitution to deceive Americans and Europeans.

The government claimed that he made a democratic atmosphere. But the reverse is true.for example, CPJ (Committee of protecting Journalists) said on December 2013, ``Ethiopia is the second ranked country from the world by imprisoning and disturbing journalists.`` according to CPJ, Eskinder Nega, Riyot Alemu, and Wubshet Taye from Journalists. And Andualem Arage and many others from political partiesand so many party members are imprisoned. Based on these facts, there is no democracy in Ethiopia.

Democracy is a process, the regime says. You see how they are joking? Democracy is not a process rather it is a natural right of the people. So, we should have to unite and struggle for a real democracy in our motherland!

# We can reconcile

**Yoseph Teklu/ Fulda**

The problem of Ethiopia is not with the flag the soil the mountain desert or the hills; it is with the narrow minded thinking and actions of few Ethiopians who should not be able to bully everyone else like an abusive husband or father who pushes his family out of their legitimate home. Such an abuser needs to be stopped and held accountable.

It is time for all the oppressed people to confront the bullies' ethnic hatred individuals and exploiters of Ethiopia no matter what ethnic group region or political party they represent even our own. Unfortunately it is easy for the oppressed to become the next oppressors. Instead, we need to address the root problem of injustice by creating an attitude that values and includes all people and groups as valuable members of our society. To do this, we must uphold the rule of law and policies that protect all of us from ourselves.

Admittedly, we have a lot of work to do to change our situation, but the spirit of discontent ethnic hatred/division is spreading across Ethiopia and many are motivated in ways never seen before. We need to work hand in hand with other Ethiopians in acknowledging either the wrongful acts committed against us or the wrongful acts we have committed to others. So, we can reconcile and live in harmony with each other.

# We need a united struggle

**Aster Gebremariam/Bayreuth**

We, as people from different ethnic groups of Ethiopia have more in common to unite us than divide us. If we concentrate on that commonality, we could free our people and our country.

Our history indicates that we have been isolated from each other, fighting the same opponent, but doing it alone. We have been doing it haphazardly and mostly ineffectually, from many various fronts. The evidence of our frustration is in the many years of our struggle. As long as we fight our battles alone, we will not win the war. Instead, we are not only prolonging the suffering of our people, but we are actually contributing to the destruction of everyone who lives in Ethiopia. We know that what the ethnic apartheid regime of the TPLF/EPRDF fears the most is unity within our ethnic groups and unity among differing ethnic groups. Think what could happen if the Oromo, being the majority ethnic group, became united as one so they could speak with one voice. Think about what could happen if the Oromo's joined with other ethnic groups! Our victory could be more certain than ever.

Think what it will take to sustain that victory for the future generations who we would

want to live in peace and harmony with their neighbors. To win such a battle for lasting justice, we have to first think differently (by putting our humanity before ethnicity or anything) and then do things differently. This is what I have been talking about. May God bless all the beautiful people of Ethiopia and enable them to become soldiers of love, justice, equality.

# Land grabs and repression in Ethiopia

**Zeki Kerim, Abdi / Fulda**

The current and potential foreign investors in Ethiopia need to understand, that they are doing business with an unelected regime that took power by force, manipulation and corruption. The TPLF/EPRDF regime has no legitimate authority to negotiate with the name of the Ethiopian people. It is risky to partner with a regime whose right to govern is being challenged by the majority of the people. Once this ethnic apartheid regime of the TPLF falls or implodes, these agreements of land grabs will not be binding.

In the other hand injustice and repression is very high in the same country Ethiopia. To challenge such kind of inhuman treatments, we Ethiopians should have to pay a sacrifice and committed to do our best for our future country. We must not to inherit our children a devastated land. Let`s stand up together! Ethiopia should prevail.

# Struggle for justice

**Misrak Tesfay/ Schlüchtern**

We are on struggle to bring justice, freedom, equality, unity and peacein Ethiopia. We must be free from tribalism, the easy marginalization of others and attitudes that make us not care about the barefoot child from the Ogaden, the Oromo teen sleeping on streets, the Amhara Orphan or the displaced subsistence of Gambella farmers or other farmers all over Ethiopia.if we want to break the insane circle,we must start from ourselves.

The pain of our people throughout Ethiopia should give us the foundation for working together until all are free. Let this be a beginning of people appreciating each other as human beings; regardless of religion gender political view or other differences.

May God help us become humble and and example to others. So together we can improve the lives of our people and ourselves.

# Unity is power

**Elsa Diriba/ Fulda**

Unity is essential for our mutual survival. Even the ethnic apartheid regime of the TPLF/ EPRDF uses segregation to prolong his control. So why don`t we do the same in a productive way to bring about our shared freedom? Even if some regions of the country end up separating, they will still the rest of us.

We need to come together to protect the interests of our land and we need each other to do it. Let`s be humble and become an example to others. So together we can improve the lives of our people and ourselves.

The people should be the ones to choose their government rather than the government establishing itself by oppressing the people.

There is no time to give up on our precious people or beautiful country; despite the difficulties, for otherwise, we may end up becoming the next Rwanda or Somalia like our brother from the ogaden region stated.

# Free prisoners of conscience

**Bisrat Girir/Bisrat Weldemikael/ Aßlar**

Eskinder Nega, Wubshet Taye and many of their co-Prisoners were victims of Ethiopia's flawed Justice System and it can only be corrected by fixing the whole system, in simple terms, by making Ethiopia fully democratic. Just as the judicial branch of the regime itself, the crimes fabricated by regime mouth pieces and used against Wubshet, like collaboration and fraternization with a terrorist organization were very loosely defined if not absolutely manufactured by elements of the ruling thugs.

Denying one a medical care and starving people to death for reasons of political incorrectness was if anything very rarely used after history condemned the Nazis to a political oblivion from which they would never reemerge and this goes parallel to that. I never heard of any justice system that is too sympathetic to the regime except Ethiopia's—where even the Constitution would have to be revisited and if need be a New legislation would have to be cooked up overnight to incriminate someone who was already in prison—Siyye Abraha's case and most recently, Melaku Fanta'S are good examples. In Siyye's case, Colonel Zenawi had summoned his rubber stamp Parliament overnight and forced pass a new Form of Anti-corruption law, specifically meant to punish Siyye and in Melaku's case, the House of Federation (Ethiopia's upper House) had ruled that the defendant's case could not be appealed to the Supreme Court because they felt if the regime fails to win the case, it couldn't be appealed.

In all cases the courts granted the regime all its requests and Siyye was convicted in an absolutely manufactured political case and Melaku would also very likely be convicted because the courts lack any teeth to resist the regime's pressure or the Judges themselves could be ruling party members or sympathizers. Asked by an International press why a new legislation was required to punish inmates already in jail, Colonel Zenawi responded at the time saying" Extraordinary cases require extraordinary responses and that was what we did.

Indeed, it was extraordinary not because Zenawi cared if Siyye stole billions as Corruption was one of the defining traits of the regime, but it was extraordinary because if Siyye was allowed to abscond, the political price the regime might pay was significant and Zenawi knew that. As long Ethiopia remains undemocratic, and you believe in living for your conscience, the answer remains unthinkable!

# Love is the only Weapon!

**Murad Awel Hadju/ Fulda**

We need a new Ethiopia where no one or ethnic group claims they are more Ethiopian or less Ethiopian than the other. It is our blood and humanity which unites us not the lines of Ethiopia on a map. Anyone who live within the boarders have equal claim based on the Ethiopian soil upon which they live , not because they are a member of any one dominant ethnic group like Oromo, Amhara or Tigray.

We are all Ethiopians. We are all Africans. we are all human beings. We should be concentrating on that. It is our mother land which defines us and gives us a sense of place not the lines on a map that demarcating Ethiopia.

Once again, if we want to survive as a people, we have to put our humanity before ethnicity. This is the only way we can become greater country.

To accomplish this, you have to start by loving and accepting yourselves as God loves you. So that you can better love your families your communities your ethnic group your country and all of humanity as equally worthy of love and care. We can defeat all this injustice only with one weapon and that weapon is love.

I believe this is the only way to stop ethnic apartheid regime of TPLF that triumphs over us by singling each of us out, fighting us one at a time. Instead, we must join together, caring for each other. This is what Ethiopia lacks. This is what Africa lacks.

# Stop land grabbing!

**Mahider Geberegzi/ Wölfersheim**

For those who are far from the reality, watch the ads and articles well founded by the owners of the new vast, fertile and green land in Ethiopia and other southern countries; land grabbing doesn`t make big sense. But for the farmers of southern and western Ethiopia regions, the reality is quite different.

The unconstitutional Ethiopian ``government ``land policy started in the late 2005. It may be the most painful tragedy of their life, they can ever tell, if they are infact allowed to tell.
The suffering is very normal in Oromiya, Benishangul, Ethio-Somali and Gambella regions.

The problem is going worse to worst. The result of inequitable land acquisition better called by`` neo-colonial land grabing`` of Arab and Asia investors. This act is worsening the already broken food security situation in Ethiopia.
The peasants are losing their lands, which they own for centuries. The draconian proclamations and the brutal police force behind the mess is a point to be taken.

Officials of the Ethiopian ``government`` has already acknowledged the land grabbers by giving a license as a commercial investors. Even if the problem has started at the beginning of the $19^{th}$ century, the danger is very clear in this barbaric regime of the country.

The 1995 FDRE constitution is failed to restore any tangible land ownership right. That is why: the officials of the regime would use the article to make very huge corruption money. Land should be privately owned property in Ethiopia!

# National reconciliation

**Binyam Ekubye Teka/Fulda**

Significant and specific steps must be taken to bring about the reconciliation and unity about which we are talking. National reconciliation conference must be called to bring together neutral experts in the areas of conflict resolution and reconciliation who can provide the guidance structure training and a safe atmosphere where reconciliation can begin between our many groups.

If we could come together and admit how we have hurt or wronged others, sincerely seeking their forgiveness, we may start the process of reconciliation. None of us is without fault as we are imperfect people. However, as imperfect people, we still can start such a healing process, but we must be willing to actively pursue it.with this stand, please know that neither will it be a perfect process, but it will be a starting point towards restoration of relationships that could give us Ethiopians hope for a different Ethiopia.

It will not be easy, yet, if we put in a sustained effort, we may find reconciliation beyond what we thought was ever possible. As we do, we will be much better prepared for negotiations with anyone, even the TPLF/EPRDF regime.

## BOB MARLEY best song for Mama Africa

Africa, unite
'cause we're moving right out of babylon
And we're going to our father's land

How good and how pleasant it would be
Before God and man, yeah
To see the unification of all africans, yeah
As it's been said already let it be done, yeah
We are the children of the rastaman
We are the children of the higher man

Africa, unite 'cause the children wanna come home
Africa, unite 'cause we're moving right out of babylon
And we're grooving to our father's land

How good and how pleasant it would be
Before God and man
To see the unification of all rastaman, yeah

As it's been said already let it be done, yeah
I tell you who we are under the sun
We are the children of the rastaman
We are the children of the higher man

So, africa, unite, africa, unite
Unite for the benefit of your people
Unite for it's later than you think

Unite for the benefit of your children
Unite for it's later than you think
Africa awaits it's creators, africa awaiting it's creators
Africa, you're my forefather cornerstone
Unite for the africans abroad, unite for the africans a yard
**Africa, unite**

# ይፈለጋል!

# Wanted!



## ኦሞትኦባንግ ኦሉም

## Omot Obang Olum

**ወንጀሉ፤** በዘር ማጥፋት፣ በሰብዓዊ ፍጡር ላይ በተደረገ ወንጀል፣ በግድያ፣ በሙስና፣ ዜጎችን በማፈናቀል፣ በመሬት ነጠቃ፣ እና ሌሎች ወንጀሎች!

ጎልጉል፡የድረገጽ ጋዜጣ
www.goolgule.com

In a statement made by **Gambella** Regional governor, **Omot Olum** on ESAT [Ethiopian Satellite TV] on Friday, March 8, 2013, he said, " Anyone who broke the law in Ethiopia could be killed whether an Ethiopian or an American!"

**Master Planner of the Anuak Genocide is now out of Ethiopia and seeking an asylum somewhere in the world.**




# ጥላ መፅሄት አስረኛ እትም!

ጥላ መፅሄት አስረኛ እትሟን ይዛ May 15/2014 ለንባብ ትበቃለች። ስለዚህ አዳዲስና ነባር ደንበኞቻችን በተለመደው አድራሻችን ታገኙናላችሁ። በመፅሄታችን ላይ ያላችሁን አስተያየትና መልዕክቶች ሁሉ እስከ May 10/2014 ድረስ ልታደርሱን ትችላላችሁ። ለበለጠ መረጃ የስልክ መስመራችንን መጠቀም ይቻላል።

wir sind immer für sie da!

**አድራሻችን፡-**

**Mesfin Abraha**
**An der Obergeis 1**
**36251 Bad Hersfeld**

**tilamagazine@yahoo.de**
**tilamagazine.yolasite.com**

**Tel. 0176 5938 4456**
**015222195567**
**0176 71668780**

**TILA MAGAZIN IST EURE MAGAZIN!**